# የፊልደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን

አንድ ወንድም ሄዶ፡ ትልቅ ትኩስ የቸሪ ፓይ አምጥቶልኛል። ልንገራችሁ፡ ፍንጭ ሰጪ ነው። እንዲህ አለ፡ “ወይ ጉድ… ” ወንድም ኔቪል፡ ምን ይመስልሃል? ይኸውልህ። አያችሁ? ቼሪ ፓይ ምርጫዬ ይመስለኛል። በጣም ጥሩ ነው። እንዳልኳችሁም ቼሪ ፓይ ስትበሉ፡ አንዳንዴ፡ ፍሬው ያጋጥማችኋል። ያኔ፡ ፓዩን—አልጥለውም፡ በቀላሉ ፍሬውን እጥልና ቼሪ ፓዩን መብላት እቀጥላለው።

2 ስለነዚህ እናንተም መልዕክቶቹ ላይ እንዲሁ እንድታደርጉ እፈልጋለሁ። ስትቾኩሉ… ግድ የላችሁም እንሰማማ፡ በደንብ ማኘክ የማ—የማትችሉትን ነገር ሲገጥማችሁ፡ ያኔ፡ በቃ፡ ተዉት… ሁሉንም ነገር እንዲሁ አትጣሉ፡ ያንን ነገር (ፍሬውን) ብቻ ጣሉት፡ እና ፓዩን መብላታችሁን ቀጥሉ። ለምን፡ እንዴ አውቃችሁታል። ኧሃ-ሃም።

3 እንዲሁም… የተጠበሰ ዶሮ፡ ዶሮ ትወዳላችሁ? ሁሉም ሰው ይወዳል ማለት ይቻላል። መልካም፡ እንግዲህ፡ ዶሮ ስትበሉ፡ አጥንቱን ታገኛላችሁ፡ አጥንቱን ብቻ ትጥላላችሁ እንጂ፡ ዶሮውን አትጥሉትም። አጥንቱን ጥለህ፡ ዶሮ መብላትህን ትቀጥላለህ። ልክ አይደለም’ዴ፡ ፓት?

4 መልካም፡ በውስጡ አጥንት ወይም ዘር የሌለው ምግብ መብላት ስለምንችል ደስተኞች ነን። ሙሉ በሙሉ በሰማይ ጣዕም የተለወሰ፡ “መና” የተባለ፡ ዋፈርስ ከሰማይ ወርዶልናል።

5 ታውቃላችሁ፡ አንድ ግዜ “አለት ውስጥ እንዳለ ማር ይመስላል፡” በማለት የተናገረው ዳዊት ይመስለኛል። እንደሚመስለኝ ግጥሙ “አለት ውስጥ እንዳለ ማር፡” ይላል። ወንድሜ፡ ሆይ፡ ቀምሰህ ታውቃለህ… ተመልከተው… እንደው… ጣዕሙ አለት ውስጥ እንዳለ ማር ነው። “አለት ውስጥ እንዳለ ማር ነው፡ ወንድሜ።” እንደዚያ ነው።

6 አሁን፡ ታውቃላቹ፡ በአንድ ወቅት “አለት ውስጥ ያለ ማር።” ማለት—ምን ማለት እንደሆነ አስብ ነበር። እናም “መልካም፡ ምናልባት አንድ ጊዜ አለት ውስጥ የንብ ቀፎ አግኝተው ይሆናል፡” ብዬ አስቤ አውቃለሁ። በኋላ ሳውቀው ግን፡ ትንሽ መገለጥ አገኘሁበት። … ያን ጊዜ ፈልጌው አይደለም፡ በኋላ ግን አንዳች ነገር ተረዳሁ በጎች የሚጠብቁ እረኞች ሁሉ… ታውቃላችሁ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሆነ ነገር አለ፡ሰውነታችን የተሰራው ከምድር አፈር ነው። ህይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ—ሁሉም የመጡት ከምድር ነው። እና እነዚያ እረኞች፡ በጎቻቸው ሲታመሙ ወይም የሆነ ነገር ሲገጥማቸው ኖራ በጎቹን እንደሚረዳቸው፡ ወይም፡ የሆነ ነገር ያገኙበታል፡ ብለው ያምኑ ነበር። እና አለቱን ያሰልሷቸዋል። በጎች ያንን ሲያደርጉ፡ ዓለት ሰሊሱ አይታችኋል። እና በጎቹ ዐለቱን እንዲልሱት፡ ዓለቱ ላይ ጥቂት ማር ያፈሱበታ። እናም በጉ ማሩን ሊሊስ ሄዶ፡ ማሩን በሚልስ ወቅት፡ አያችሁ፡ በዛው—በዛው አለቱንም ይልሰዋል።

7 እንግዲህ፡ እኛም ሻንጣ ሙሉ የተጻፈ ማር እዚህ አለልን። ዓለቱ ላይ እናፈሰዋለን፡ ዓለት ላይ፡ ክርስቶስ ኢየሱስ ላይ እንጂ፡ የትኛውም ቤተክርስቲያን

ላይ አይደለም። እናንተም በጎች ሆይ አሁን ሄዳችሁ ላሱት፡ ወዲያውኑ እ—እ—እ—እንደሚያድናችሁ እርግጠኛ ነኝ። ዓለቱን ስትልሱ—ስትልሱት የኃጢያት ችግሮች ሁሉ ይወገዳሉ። ማድረግ ያለባችሁ ያ ብቻ ነው።

8 አለት ለየት የሚያደርገው ነገር ፈውሰ መያዙ ነው፡ ፈውሰ። በድሮ ዘመን፡ የራቢሰ ክትባት ከማግኘታቸው በፊት፡ “ማድሰቶን” የሚሉት ነገር ነበራቸው። አንድ ሰው ባበደ ውሻ ከተነከሰ፡ ወዲያው፡ በዚህ ማድሰቶን ላይ ያሰቀምጡት ነበር። እናም፡ ማድሰቶኑ ጋር... ከማድሰቶኑ ጋር ከተጣበቀ፡ ይሻለዋል፡ ካልተጣበቀ ግን፡ በሽተኛው በጣም የባሰበት ነው፡ ሰለዚህ—ይሞታል ማለት ነው።

9 ሰለዚህ ዛሬም እንደዚያ ነው። እኔ የማውቀው ከባዱ ንክሻ የእብድ ውሻ ሳይሆን፡ የዲያብሎሰ ነው። ሰለዚህም የዘመናት ዓለት፡ ዓለቱ አለልን። እሱ ብቻ ይኑራችሁ፡ እሱን እሰከያዛችሁ ድረሰ፡ ደህና ትሆናላችሁ። በጭራሽ እንዳትለዩት ወደ ኋላም እንዳትመለሱ፡ ጸንታችሁ ያዙት። በእርሱ ዘንድ ተጣበቁ፡ እና—እና እናንተም—ደህና ትሆናላችሁ።

10 አሁን ወደ ምሽት ትምህርታችን ከመግባታችን በፊት፡ እና—ከቻልን፡ ለጸሎት ቃል ትንሽ ጊዜ፡ መቆም እንፈልጋለን።

11 አንቺ የሮበርት ዳገርቲ እህት አይደለሽም፡ አይደል? እዚህ ጋር። ይመሰለኛል፡ ትናንት ደውላልኝ ነበር፡ እና ጸሎት እንደምትፈልግ እየነገረችኝ ነበር። እንጃ እኔ—አላውቅም፡ እሷን ትመሰያለሽ፡ እሷ መሆንሽን ወይም አለመሆንሽን አላውቅም። ባለፈው ምሽት እዚህ አይቼሻለው።

12 አሁን፡ በእግዚአብሔር ፊት መታወሰ የምትፈልጉ፡ ወይም እግዚአብሔር እንዲያሰባችሁ የሚትፈልጉ፡ ሰንቶች ናችሁ? በቃ...

13 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ በቺካጎ የሚገኘው... የመዝሙር መሪያችን፡ “እንባ ሲፈሰ ጊዜ አሰበኝ፡” እያለ ሲዘምር እንደነበረው፡ ጌታ ሆይ አሁን አሰበኝ። በሞት ሰዓት፡ በህይወት... ሙላት ላይ፡ ጌታ ሆይ፡ እንድታሰበን እንፈልጋለን። እንደ ማንነታችን፡ እንደ ኃጢያተኞች ሳይሆን፡ እንደተናዘዙ ክርሰትያኖች እንድታሰበን እንፈልጋለን፡ ልጅህን፡ እና አዳኛችንን፡ ኢየሱሰ ክርሰቶሰን፡ ሰለ... ኃጢአታችን ማሰተሰሪያ እንደተቀበልነው አሰበን። እሱም፡ ያለን ብቸኛው—ብቸኛው ድላችን፡ ብቸኛው መንገድ፡ ብቸኛው የመዳን መንገድ እንደሆነ እናውቃለን። በማናቸውም ቤተ ክርሰቲያን ወይም በማናቸውም መካኒካል መሳሪያ-ዎች፡ ወይም በማንኛውም ድርጅት አይደለም፡ ነገር ግን በኢየሱሰ ክርሰቶሰ፡ እና በሱ ብቻ ነው።

14 ሰለዚህ ራሳችንን አንድ ላይ እንደተሰበሰብን፡ ዛሬ ማታ እንድትባርከን ወደ አንተ ሰንለምን በጉያህ የተዘጋጀልንን፡ ቃልህን ለማጥናት እና ለማወቅ በሰሙ እንቀርባለን። ሕያው ለሆነች ቤተክርሰቲያን መንፈሳዊ—ሰውነታችንን እንድንገነባ ዘንድ። በህዝብህ መካከል ለምትሄድባት፡ ለምትኖርባት፡ ለምትመላለሰባት፡ እና ምቾት ለምታገኝባት ቤተ ክርሰቲያን፡ ምን ማድረግ እንዳለብን ለምትነግረን፡ እና ወዲያውኑ ማድረግን ለምናውቅባት።

15 እና አባት ሆይ፡ እንወድሃለን፡ ነገር ግን እንደፈለክ በእኛ በኩል መናገር የምትችልበት አቋም ላይ ገና እንዳልደረሰን እናውቃለን። ሰለዚህ እንድትገረዝን፡ ማለትም፡ ሰንፍናችንን በሙሉ እንድታርቅልን፡ ትርፍ የሆነውን

ሰጋችንን ዛሬ ከእኛ እንድትቆርጠው እንጸልያለን፡ ይህም ሙሉ በሙሉ ለአንተ የተሰጡ፡ በማንኛውም ጊዜ የምትጠቀምባቸው እነሆን ዘንድ ነው። አባት ሆይ፡ ጊዜው ዛሬ ምሽት እንዲሆን እንጸልያለን፡ እነዚህን እንቁዎች ከመፅሃፍ ቅዱስ አውጥተን በደንብ እንድናጠራቸው እና ህዝቡም በዚህ ታላቅ የቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ የክርስቶስን ነፀብራቅ እንዲያይ ተጠቀምብን። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

16 አሁን፡ እስከ ዛሬ ምሽት የቤተ ክርስቲያን ዘመን ድረስ፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመናትን አይተናል፡ ይህ ስድስተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ነው። ነገ ማታ የቤተክርስቲያንን ዘመናትን መጨረሻ እናያለን፡ ከሰኞ እስከ እሑድ፡ በየምሽቱ አንድ አንድ አይተናል። እና የዛሬው፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመንም የፊልደልፊያ ቤተ ክርስያን ዘመን ይባላል። እናም ኮከቡ ወይም መልእክተኛው፡ የ— የዛች ቤተ ክርስቲያን ዘመን መልአክ-መልእክተኛ፡ ጆን ዌስሊ እንደሆነ፡ ሳንጠራጠር፡ በሚሉ ልባችን፡ እናምናለን። ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሚጀምረው በሉተራን ቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍጻሜ በ1750 ሲሆን፡ እስከ 1900 ድረስ፡ የዌስሊያን ቤተ ክርስቲያን ዘመን እስከ 1906 **ዓ.ም**. አካባቢ፡ ቆየች። ከዚያ በመቀጠልም፡ ሎዶቅያ፡ ተከተለች።

17 አሁንም ይህ… ቤተ ክርስቲያን ዘመን “የወንድማማች መዋደድ” ዘመን፡ እና የታላቁ “ሚሲዮናውያን” ዘመን እና “የተከፈተ በር” ዘመን በመባል ይታወቃል። ሽልማቱም—አምድ መሆን፡ “አምድ አደርገዋለሁ፡” የሦስት ሰሞች መገለጥም፡ ማለት የእግዚአብሔር ሰም፡ የእግዚአብሔር ከተማ ሰም፡ እና የእግዚአብሔር አዲስ ሰም፡ በዚህ ዘመን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የተገለጠው መገለጥ ይህ ነው። አሁንም፡ ቤተክርስቲያኒቱ… የዚህ ዘመን ጅማሬ ከራእይ 3:7፡ እስከ ቁጥር 13 ድረስ ነው፡ ቁጥር 13ን ጨምሮ፡ ራእይ 3፡7 እስከ 13።

18 እንግዲህ፡ ወደ ኋላ ተመልሰን፡ ከባለፈው ማታ ጀምረን እነዚህን ስንገመግም ቆይተናል። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጀማሪ፡ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመን ናት። የዚያች ቤተ ክርስቲያን ዘመን መልአክ ወይም ብርሃን (አገልጋይ) ማን እንደ ሆነ መናገር ትችላላችሁ? ጳውሎስ ነው። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ከ 55 እስከ 170 **ዓ.ም**. ድረስ ነበረች። ከ 55 የመርጥኩበት ምክንያት፡ ሚሽነሪ ጉዞ የጀመረበት ያኔ ስለነበረ ነው። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን እና—በዙርያ የነበሩ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የመሰረታቸውም ያን ጊዜ ነበረ።

19 መልካም፡ ሁለተኛ የቤተክርስቲያን ዘመን ሰምርኔስ ናት። ከዚህ ክፍል ውስጥ፡ የዚያ ቤተ ክርስቲያን መልአክ ማን እንደነበረ የሚያስታውስ ሰው አለ? ኢራኔዎስ ነው፡ ትክክል። መልካም፡ ከ170 እስከ 312 ይዘልቃል።

20 ሦስተኛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን የጴርጋሞስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። በክፍሉ ውስጥ፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን ቅዱስ ማን እንደነበረ፡ ማስታወስ የሚችል ሰው አለ? ቅዱስ ማርቲን ነው፡ ትክክል። ከ312 እስከ 606።

21 ከዚያም የሚቀጥለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ትያጥሮን ናት። የዚያን ዘመን መልአክ ቅዱሱንና መልእክተኛውን፡ የሚያስታውስ አለን? ኮሉምባ ነው፡ ትክክል። ይህ ደግሞ ከ606 እስከ ‘515 ነው።

22 ቀጣይዋ ቤተ ክርስቲያን፡ የትናንት ምሽት ዘመን ማለትም ሰርዴስ ናት። መልአኩን የሚያውቅ... ያለጥርጥር፡ የዚያን ቤተ ክርስቲታን ዘመን ታውቁታላችሁ። አስታወሳችሁ? ማርቲን ሉተር ነው። ዘመኑም ከ1520 ጀምሮ እስከ 1750 ነበር።

23 ዛሬ ማታም የፊልደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ላይ ነን፡ የዘመኑ መልእክተኛ፡ ጆን ዌስሊ ነው። ከ 1750 እስከ 1906 **ዓ.ም.**፡ ዘመኑም “የወንድማማች መዋደድ” ወቅት ነው።

24 እንግዲህ፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት እያንዳንዳቸው፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ባሕርያት እንደገለጹ ተረድተናል። ያ—ያም ቤተ ክርስቲያን ምን እንደ ነበረች እና የቤተ ክርስቲያንን ባሕርይ ይናገራሉ፡ ማለት፡ የቤተ ክርስቲያንን፡ ባሕርያት ተናግሯል።

25 እንግዲህ፡ ትናንት ማታ ማርቲን ሉተር ነበረ። እኔም... በዚህ ውስጥ፡ እንደ እኔ... ይህን ያመጣሁበት እና ልጆቹ በቴፕ ላይ የሚቀዱበት ምክንያት... ቀኑን ሙሉ ሳጠና እውላለሁ። መቼም እናንተም ትሉኛላችሁ፡ “እዚህ የምታቀርባት ትኻሽዬ ታሪክ ቀኑን ሙሉ ትላለህን? ” አይደለም። ታሪካዊ ነጥቦቹ በመጽሐፉ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡ እሺ። እንደ እኔ; ይህ ነገር... እዚህ የመድረስ ምክንያት፡ እነዚህን ነገሮች በመንፈስ ምሪት በፊታችሁ ማውጣት ነው፡ በዚያም መሰብሰባችን የመገለጥ ክፍሉን ለማግኘት ነው። ታሪኩን ከሆነ፡ ከመጽሐፉ ውስጥ ማንበበ ይቻላል። መገለጡን የማገኘው ግን ከዚህ ነው፡ ከዚያም ከቅጂው ለቅመን እናወጣለን። ከዚያም በ—በመጽሐፍ መልክ... እናዘጋጃለን፡ ከዛ በኋላ፡ እዚህ በሰማያዊ ሰፍራ በክርስቶስ ኢየሱስ በሕብረት ሆነን የተሰጠን ከመንፈስ ቅዱስ ያገኘነው የመንፈሳዊ መገለጥ ክፍል፡ እና ታሪካዊ ዳራውን ሁለቱ ይኖረናል። እናም በእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ላይ እነሰ ያለች አስገራሚ ማብራሪያ መጽሐፍ እንደሚሰራበት አምናለሁ። ጌታም በረከቱን ይሰጥ።

26 እንግዲህ፡ የ... ትናንት ማታ፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የ... **የሰርዴስ** ቤተ ክርስቲያን ዘመን ሰትሆን፡ በግሪክኛ ትርጉሟ፡ “ያመለጠ፡” በኢንግሊዘኛ ግን “የሞተ” የሚል ትርጉም ያለው ይመስለኛል። ስለዚህ፡ “የሞተ” ቤተ ክርስቲያን እና “ያመለጠ” የሚል ድርብ ትርጉም ነበረው ምክንያቱም በዚያ በ1500፡ ወይም በ1520 በጳጳሳዊ አገዛዝ ዘመን የሞተች ቤተ ክርስቲያን ናትና፡ ይህም—የጨለማው ዘመን ብለን የምንጠራው ታላቁ ጽጽሰና አገዛዝ ዘመን ነበር፡ ክርስትና ከመቼውም ጊዜ በላይ፡ ከሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ዘመን እንኳ ሳይቀር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ዘመን ነው።

27 ሌላው፡ አንድ የሚያስደንቀው ነገር አለ፡ ነገር ግን እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት የሚጀምሩትን ነገር አሰቡት፡ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ዘመን የተጀመረው ማንኛውም ነገር በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘመን ያልፋል፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን በሌላኛው ላይ እየተደረበ መምጣጡ አስታውሱ። ታሪኩን ከመጽሐፉ ጋር በደንብ ካጠናችሁ፡ ትደርሱበታላችሁ።

28 አንዳቸው በአንዳቸው ላይ፡ **እንዲህ** የተደራረቡ አይነት ናቸው። እና አንድ የቤተክርስቲያን ዘመን ሰያበቃላት፡ በዚያም መካከል የሚመጣ መልአክ ያቺን

ቤተ ክርስቲያን አንድ ጊዜ ያጣችውን እምነት ወደ ኋላ ለመጥራት ነው። ሁልጊዜ እንደዚያ ነበር።

29 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የመጨረሻውን መጽሐፍ ይሁዳ ላይ፡ መገለጡን እስክታገኙት ድረስ፡ ተመልከቱት። ይሁዳ እንዳለው፡ "ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ እምነት እንድትጋደሉ ጻፍሁ—ጽፌላችኋለሁ።" በሐዋርያትና በራእይ መምጣት መካከል፡ መደረቢያው እሱ ነው፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ ሐዋርያት ሞተዋል። አያችሁ፡ ሄደዋል አልነበሩም። በዚያን ጊዜ በህይወት የነበረው፡ ቅዱስ ዮሐንስ፡ ዘመለኮት ብቻ ነው፡ እርሱም የራዕይ መጽሐፍን ለመጻፍ ከጌታ መልአክ መገለጥ የተቀበለ ገላጭ ወይም ጸሐፊ ነው።

30 አያችሁ፡ አሁን፡ አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ይደረባሉ። ስለዚህ እናንተም... ከዚህ በፊት፡ ሰገልጸው እንደቆየሁ፡ ያንን አስተውላችሁ እንደያዛችሁት አስባለሁ። እንደው እዚህ ውስጥም—የ **ሰርዴስ** ዘመን፡ የጋብቻ ዘመን ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ፡ ቤተ ክርስቲያን እስከ ትያጥሮን ድረስ ወደ ሙሉ ሕልውና አልመጣችም፡ በሰርዴስ ግን ተጋባች። **ሰርዴስ** ማለትም "በጋብቻ ውስጥ—መሆን ነው።"

31 አሁን—አሁን ካስተዋላችሁት **እዚህ** ተጋባች፡ እና **ወደዛ** ዘመን ተደረበች። እና ሉተርን ትናንት ማታ፡ ሉተርን ካስተዋላችሁት፡ "የሞተ" ስም ይዞ ወጣ፡ የሙታን ስም፡ እና "ያመለጠች።" አያችሁ፡ **ከዚያ** ጀርባ የሞተች ቤተ ክርስቲያን ነበረችው፡ እና **እዚህ** ዘመን ላይ ደግሞ ጥቂት ያመለጡ ቅሪቶች ወጡ።

32 እናም ዛሬ ምሽት የፊላዴልፊያን ዘመን ስናጠናቅቅ፡ የሎዶቅያ ዘመን መጀመሪያን ያመጣል።

33 ከዚያ ነገ ማታ በማጠናቀቂያው ላይ... በመጨረሻ ላይ፡ አስተውሉ፡ መልአኩ የሚገለጠው ሊያልቅ ሲል ነው (ማለት በዘመን ፍጻሜ ላይ) ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ፍቅሯን በማጣቷ እና በዚህ ሁሉ ዘመናት ያደረጉትን ከእግዚአብሔር እንዴት እንደራቀች፡ ይወቅሳታል። እና፡ በዚያን ጊዜ፡ ቤተክርስቲያኗን ወደ ቤት ለመውሰድ ንጥቀት ይመጣል፡ በመልእክቱ ጊዜ ቤተክርስቲያን ትሄዳለች። እኛም አሁን—ያንን ዘመን እየተቃረብን ነው። ገብቷችኋል? መልካም። አያችሁ? መልካም። እዩት፡ (የዘመኑ መልእክተኛ)—የቤተ ክርስቲያኒቱ መልአክ የመጀመሪያ ፍቅራቸውን በመተዋቸው ሊገሰጻቸው፡ ሊያመጣቸው... እና ሊመልሳቸው በሚመጣ ጊዜ ይህ ይሆናል።

34 በዚህ ምሽትም መልእክተኛው ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡ የመልእክ-መልእክተኛ (እያንዳንዱ ዘመን እንደዛ) ስለ ስራቸው ሁሉ ሊገሥጽላቸው ተመልሶ ይመጣል። ስለዚህ በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ መደራረብ ይኖራል፡ ልክ እንደዚያ እርስ በእርሳቸዉ ይደራረባሉ። ልክ ደረጃ እንደ መውጣት፡ **እንደዚያ፡** ወደላይ እንደመውጣት አንዱ በአንዱ ይደራረባል።

35 አሁንም በዛሬ ምሽት መልእክተኛ፡ በጆን ዌስሊ ላይ ቀንጨብ ተደርጎ የወጣ አጭር ታሪክ ይዣለሁ። ጆን ዌስሊ የዘመኑ ኮከብ ነበረ። እናም ሰኔ 17 ቀን፡ 1703፡ በኤፕዎርዝ ሬክተሪ፡ እንግሊዝ አገር ተወለደ። ከአሥራ ዘጠኝ ልጆች አሥራ አምስተኛው ልጅ ነበር። አባት እና እናቱ፡ ጆን እና ሱዛና ዌስሊ

ይባላሉ። አባቱ፡ ሰባኪ፡ እናቱም፡ የተሰጠች ቅዱሰት ሴት ነበረች፡ እንኳን አሥራ ዘጠኝ ልጆች ቢኖሯትም፡ በሚኖራት የተጣበበ ቀን ውስጥ ልጆቿን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችንና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ለማስተማር እና ለመጸለይ ብዙ ጊዜ ታገኛለች። ወንዶቹ የሆኑትን እንዲሆኑ ያስቻላቸው ነገር ያ ነበር። ወንድሙ፡ የመዝሙር ደራሲ፡ ቻርልስ፡ እስካሁን በዓለም ካየናቸው እጅግ የተቀቡ መዝሙሮች ብዙ ያበረከተ ሰው ነው።

36 ጆን፡ የጆርጅ ዋይትፊልድ ረዳት ነበረ። ጆን—ጆን ዌስሊ እና ጆርጅ—ጆርጅ ዋይትፊልድ በእውነቱ የሜቶዲስት… ወይም የቅድሰና ትምህርት መሰራቾች ነበሩ።

37 ጆን ለሰልሳ አመታት፡ በየማለዳው አራት ሰዓት ላይ ማልዶ ይነሣ ነበር። ቤተ ክርስቲያን የወደቀችበት አንድ ነገር ይህ ነው። በየማለዳው አራት ሰዓት እየተነሳ፡ ለሃምሳ አመታት ያለማቋረጥ አምስት ሰዓት **ጠዋት** ላይ ይሰብክ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በቀን ከሁለት እስከ አራት ጊዜ ይሰብክ ነበር። በእንግሊዝ ሰዎች፡ እንዲህ ይነገራል፡ "ወንጌልን ለመሰበክ በየአመቱ፡ አራት ሺ-አምስት መቶ የእንግሊዝ ማይል በፈረስ ይጋልብ ነበር።" አራት ሺ-አምስት መቶ ማይሎች… የእንግሊዝ ማይሎች ነው፡ ከእኛ በበለጠ እንደሚረዝም፡ ታውቃላችሁ፡ ይህም ወንጌልን ለመሰበክ ነው።

38 በዘመኑ ሰለ እርሱ ሰም ማጥፋት፡ ሰድብ፡ እሱን የሚሳለቁ፡ ብዙ መጻሕፍቶች ተጽፈዋል። አሁን ግን ለረጅም ጊዜ መታሰቢያቸው ጠፍተዋል፡ ደራሲዎቻቸውም እንዲሁ። አየርን ብቻ ትጎሰማላችሁ እንጂ—የእግዚአብሔር ልጅ ተቃውማችሁ፡ ምንም ነገር ማድረግ አትችሉም። ምንም ቢሆን፡ እግዚአብሔር እንዲሁ ያሻግራቸዋል።

39 ሜቶዲሰት ተብሎ የተጠራበት ምክንያት እሱ ይጠቀምባቸው ከነበሩ ዘዴዎች በመነሳት ነው። እንደሚባለው፡ "በህይወት ዘመኑ ሁሉ፡" "ከአርባ ሺህ በላይ ሰብከቶችን መሰበኩ፡" ይነገርለታል። እሰቲ አሰቡት፡ አርባ ሺህ ሰብከቶች። ከመሄዱ ከ1791 በኋላ ብዙም ሳይቆይ፡ የሜቶዲሰት የኃይማኖት ተቋም በመሆን በዓለም ላይ ሥር ሰድዶ የሜቶዲሰት ቤተ ክርሰቲያንን ጀመረ። በእርግጥ፡ በወቅቱ፡ እነ አሰበሪ እና ሌሎች ብዙዎች በወቅቱ ነበሩ።

40 እንግዲህ፡ ለዚህች ቤተ ክርሰቲያን የተሰጠ ሰላምታ፡ ካሰተዋልነው፡ በፊላደልፊያ መልእክተኛ፡ በ 7ኛው ቁጥር አሁን እንጀምረዋለን። በውነተኛዋ ቤተክርሰቲያን—እውነተኛ ቤተ ክርሰቲያን እንደነበረች የሚባልላት ነች። በምሰክርነት እውነተኛ ቤተክርሰቲያን የተባለላት ነበረች።

### … በ**ፊልድልፍያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርሰቲያን መልአክ ጻፍ፡…**

41 አሁን እያንዳንዳችሁን፡ አሳባችሁ፡ ወደ መደረብ እንዲያተኩር እጠራችኋለሁ። እንግዲህ፡ እዚህ ደርሳችሁ፡ መልአኩ ካያችሁት… ወደ ሜቶዲሰት ዘመን ለመደረብ… በዘመኑ የመጣበት መንገድ፡ ወደ ፊላዴልፊያ… ወይም ለሎዶቅያ፡ ወደ የጴንጤቆሰጤ ዘመን ትንሽ አልፎ ሲዘልቅ ታያላችሁ። ከዚያም፡ ነገ ማታ፡ የጴንጤቆሰጤው መልእክተኛ እነዚህን በመውደቃቸው ሊገሥጽ ተመልሶ ይመጣል፡ በዚህ በሰርዴስ ዘመን (በሉተር ዘመን)፡ ልክ ሲደረቡ በመውደቃቸው ምክንያት እንደገሰጻቸው እንዲሁ ነው።

42 ወንድማማች መዋደድ። ታላቅ የሚሸነሪዎች እና የሚሸን ዘመን ነበር። ዓለም ያንን አይነት ዘመን አይታ አታውቅም፡ ወደኛ ዘመን ሳይቀር አሁን ተሻግሮ መጥቷል፡ ይህም፡ ዓለም በየቦታው እንደዚህ አይነት የሚስዮናውያን ጊዜ አለማየቷ ነው። በመጨረሻው... ኦህ፡ ባለፉትን መቶ ሃምሳ ዓመታት፡ ሚስዮናውያን በወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ ክፍሎች የወጡበት በዓለም ታሪክ ውስጥ በጣም አስደናቂ ከሆኑት ጊዜያት አንዱ ነው እላለሁ። አዎን አንዱ ነው...

43 እንደ እውነቱ ከሆነ—እንደ እውነቱ ከሆነ፡ የወንጌልን መልእክት፡ በወረቀት እና በትራክቶች እና በመጻሕፍቶች ሁሉ ሄደ፡ ወንጌል ከሰማይ በታች ባሉ ሕዝቦች ሁሉ ከገባ ቆይቷል፡ እጅግ ቆይቷል። ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ ኢየሱስ የተናገረው ያ እንዳልሆነ ይህም ማረጋገጫ ነው። “ወደ ዓለም ሁሉ ሂድ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን ክፈቱ፡” አላለምና። ወይም “ወደ ዓለም ሁሉ ይሂዱ እና ሰነ ጽሑፍን አሰራጩ፡” አላለም።

44 እነዚህ ነገሮች መልካም ቢሆኑም፡ ለቤተክርስቲያን የሰጣት ተልዕኮ ግን፡ “ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ሰበኩ ነው።” ወንጌልም ቃሉን ወደ ሕይወት ማምጣት ነው እንጂ፡ ዝም ብሎ ቃል ብቻ አይደለም። አያችሁ? ምክንያቱ ኢየሱስ እንደተናገረው፡ ወድያውኑ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡” ብሏል። ለቤተክርስቲያን የሰጣት—የመጨረሻ ተልእኮው፡ ማርቆስ 16፡ ታውቁታላችሁ፡ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።” በማቴዎስ ምዕራፍ 10 ላይ፡ ለቤተክርስቲያን የሰጣት የመጀመሪያ ተልእኮ፡ ይህ ነው፡ “ድውያንን ፈውሱ፡ ሙታንን አስነሱ፡ አጋንንትን አውጡ፡ በነጻ እንደ ተቀበላችሁ፡ በነጻ ስጡ።” ለቤተክርስቲያንም የሰጣት የመጨረሻ መልእክት፡ “ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡ ያላመነ ግን ይፈረድበታል፡ ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።”

45 ብዙዎች ያንን ክፍል እዛ ላይ ማቆማቸው አያስገርምም? **“እና”** ማለት አረፍተ ነገርን አንድ ላይ የሚያገናኝ ድልድል ነው፡ አያችሁ። እንግዲህ፡ እንደተናገረው፡ (ብዙ አገልጋዮች “ሂዱ ወንጌልን ሰበኩ፡” ይላሉ።) “ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡ ያላመነ **ግን** ይፈረድበታል፡ ምልክቶች**ም** ይከተሉአቸዋል። ያመኑት**ም፡** እነዚህ ይከተሉአ**ቸዋል።** በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ። እባቦችን ቢይዙ፡ ወይም የሚገድል ነገር ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም፡ እጃቸውን በድውዮች ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ።” የሕያው እግዚአብሔር ምልክቶች በሰዎች መካከል ይሰራል። ኦህ፡ እስከ የት አለ? ለአለም ሁሉ። ገብቷችኋል? ለመላው አለም።

46 ስለዚህ ይህ ማለቴ የጴንጤቆስጤ መልእክት እያልኩ ነው... (የጴንጤቆስጤ ድርጅት አይደለም።) የጴንጤቆስጤ መልእክት ብቸኛው እውነተኛ የእግዚአብሔር መልእክት ነው። አሁን፡ እያነበባችሁ ከሆናችሁ፡ ማርቆስ 16 ተመልከቱ። መልካም፡ እዚህ ጋር ኢየሱስ ቤተክርስያኑን ተልእኮ ሰጣት፡ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልን ሰበኩ፡ እነዚህ ምልክቶችም፡ በልሳን መናገር፡ ድውያንን መፈወስ፡ ተአምራትን ማድረግ... ” እስከ የት ድረስ ይዘልቃሉ? “ለዓለም በሙሉ።” ለ—ለሰንቶች? “ለፍጥረት ሁሉ።” ያኔ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ነው፡ “እስከ ፍጻሜ ድረስ።” መልካም። **እነዚህ**

ምልክቶች ይህንን ቤተ ክርስቲያን ብቻ ይከተላሉ? “ያመኑት፡ በዓለም ሁሉ። ዓለም ሁሉ፡ ለፍጥረት ሁሉ፡ እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል።” **ለእነዚህ** ብቻ አይልም፡ “እነርሱ” ለሚያምኑት ነው። ስለዚህ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያንን ነው። አያችሁ?

47 እንግዲህ አሁን፡ ወደዚህ ዘመን ደርሰናል፡ ዛሬ ማታ የደረስንባት ይህች የፊልደልፊያ፡ **ፊ-ል-ደ-ል፡** የፊልደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ናት። በዚያች ዘመን፡ ወንጌልን አሰፋፍተዋል ሚስዮናውያንንም ልከዋል፡ መላውን ዓለም በሥነ ጽሑፍ ሞልተዋል።

48 ኢየሱስም ያለው ግን፡ “ይህ ወንጌል ይሰበካል—ይህ **ወንጌል** ለእኔ ምስክር እንዲሆን ለዓለም ሁሉ ይሰበካል፡ ያኔ መጨረሻው ይሆናል።” እንግዲያውስ፡ ያኔ፡ የተናገረው ነገር፡ ስነ ጽሑፍ ማሰራጨት፡ የሚነበብ፡ እና የሚጻፍ፡ እንዲሁም የሒሳብ ቀመር አስይዞ ሚስዮናውያንን መላክ፡ ትራክቶችን ማስተላለፍ እና ሰዎች እጅ ለእጅ በማጨባበጥ እግዚአብሔር መኖሩን ማሳመን፡ ያ ብቻ ከነበረ፡ እንግዲያውስ የመምጣቱ ዘመን ካለፈበት ቆየ፡ ኧሃ-ሃህ። ስለዚህ ወንጌልን የሚያሳየው... ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ “ወንጌል በቃል ብቻ አልመጣም፡ በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ እንጂ።”

49 ከዚያም ኢየሱስ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ስበኩ፡” በማለት አዘዘ። እሱ የተናገረው፡ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ እና አሳዩ!” ይህ ደስ ይለኛል፡ “የወንጌልን ኃይል አሳዩ።” የተናገረው ነገር፡ ቃሉን ወሰዳችሁ፡ ለሰዎች የሚናገረውን አሳይታችሁ ኑሩት። ኦህ፡ መንገዱ ይህ ነው። ያም ያረጋግጠዋል።

50 ኦህ፡ በዓለም አቀፍ በአንደኛ ደረጃ የሚታወቅ፡ የሱዳን ሚስዮናውያን ሐላፊ፡ የሆነው ክቡር ሞሪስ ሬድሄድ፡ ቤቴ በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አንተ ባፕቲስት ስትሆን፡ እውነት ምን እንደሆነ ማወቅ ነበረብህ።”

እኔም “እውነት’ማ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡” አልኩት።

እርሱም እንዲህ አለ፡ “እንግዲህ... ” አለኝ፡ “እነዚህ ጴንጤቆስጤዎች አገኛቸው ባክህ? ”

እኔም “መንፈስ ቅዱስ ነው፡” አልኩት። አያችሁ?

እርሱም “አይ፡ የቤት ዕቃ ሲሰባብሩ ሲረጋግጡ አየኋቸው፡” አለኝ።

51 “አዎን! ብቸኛው ነገር፡ እናንተ ራሳችሁን ተጠራጣሪዎች ስለሆናችሁ እራሳችሁን ከእነርሱ ታርቃላችሁ።” መንኮራኩሩ ማሽከርከር የሚያስችል፡ እጅግ ብዙ እንፋሎት እያላቸው፡ ግን ፊሽካውን በመንፋት ያለውን ሁሉ ይጨርሱታል፡ አያችሁ። እኔ አልኩት፡ “እሷን እዚህ ጋር ቁጭ ቢያደውርጓት፡ ምልክቶች፡ ድንቆች፡ እና ተአምራቶች፡ እና ሁሉም ነገር ይኖራቸው ነበር። ነገር ግን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ፡ አንድ ቦታ ላይ መተንፈስ አለበት፡ ስለዚህም ወደ ውጪ—በመጮኽ፡ እንዲሁ ያስተነፍሱታል።”

52 እምም፡ እኔም የሚተነፍስ እንፋሎት የሌለኝ ሆኜ ከመደንዘዝ፡ እንደነሱ ባንቧርቀው ይሻለኛል። እናንተስ አይሻላችሁም? ያ ሰውዬ እንዳለው፡ “ትንሽ የዱር ላይ እንትትን ብፈራ እመርጣለሁ እንዳለ... ምንም እሳት የሌለው ከመሆን ትንሽዬ የማይታውቅ እሳት ቢኖረኝ እመርጣለሁ አለ።”

53 የዛሬው ችግር፡ የእሳት ስዕል፡ **ለመሳል** እንሞክራለን፡ “ታውቃላችሁ፡ ድሮ በጴንጤቆስጤ ግዜ፡ እንዲህ ያደርጉ **ነበር**።” እንዴ፡ በብርድ የሚንዘፈዘፍ ግለሰብን (በብርድ ለሞት የቀረበውን ሰው) የእሳትን ስዕል ማሳየቱ ምንን ይጠቅመዋል? ምንም አይጠቅመውም። በጭራሽ። ትክክለኛው እሳት ራሱ… ማግኘት አለበት። ጴንጤቆስጤዎች ለጌታ እንዲሠሩ፡ እና ምልክቶችን እና ሰራዎችን እንዲያደርጉ ያደረጋቸው የእግዚአብሔር ኃይል ካለ፡ እናንተም **ስዕሉን** መሳል ትታችሁ፡ ስዕሉን በህይወት ካመጣችሁላቸው፡ ተመሳሳይ ልምምድ፡ ተመሳሳይ መዳን ይኖራቸዋል፡ ምስክርነታቸውን ያኔ **ባደረጉት** መንገድ ያትማሉ። አያችሁ? ነገር ግን እናንተ ልታሳዩአቸው ይገባል። ወደ ሌላ ትውልድ በሆነ ቦታ ላይ ማላከክ የለባችሁም፡ ወደዚህ ማምጣት አለባችሁ።

54 አሁን ይህ የወንድማማች መዋደድ ዘመን ታላቅ የሚሰዮናውያን ዘመን እንደነበረ አይተናል። ኢየሱስም “ወደ ዓለም ሁሉ፡ እና ወደ ፍጥረት ሁሉ ሂዱ፡ እነዚህ ምልክቶች**ም** ይከተላሉ፡” ብሏል።

55 አሁን፡ በታሪክ እና በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳየነው ሁሉ፡ እስኪ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፡ በእያንዳንዱ ምሽት የሆነው ነገር… ? መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ ለዮሃንስ እንዲህ ይሆናል ብሎ የነገረው ነገር አንብበናል፡ እዚህ ጋርም ታሪክ ወስደን መርምረን መፈጸሙን አረጋግጠናል። በትክክል። እኔም እነዚያን—ሰዎች ለመመርመር ይህን ያህል ጊዜ የወሰድኩትበት ምክንያት ይህ ነው ማለት ይህ መልእክት ያስተላልፍ የነበረው የእግዚአብሔር-ባርያ ወዴት እንደ ነበረ ለማየት ነው፡ እሱ ግን እዚያው ነበረ። ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፡ እዚያው ነበረ፡ መልእክቱን ከመጀመሪያው ጀምሮ ጠብቆታል፡ በፍፁም አልቀለደበትም።

56 ከዚያ ተገፍቶ መውጣቱን አይተናል፡ ያንኑ ዘመንም “የሞተ ዘመን” ብሎታል፡ ጨለማ፡ ወዘተ ነበር። እና ከዚያ ትንሽ ብርሃን ወጣች፡ ከዚያም ትንሽ ኃይል አገኘች፡ ከዚያም ልክ በዘመን ፍጻሜ ላይ (ወደ እውነተኛ ልምምድ ውስጥ) ወደ ጴንጤቆስጤ ገባች፡ ከዚያም ሙሽራይቱ ሙሽራይቱ ትወሰዳለች፡ አትገኝም ትሄዳለች፡ ከዚያም መከራው ተመልሶ ይገባል፡ አያችሁ፡ በዓለም ሁሉ ፊት እየመጣ ያለው ታላቁ መከራ አለ።

57 እንግዲህ ዘመኑ ታላቅ የሚሰዮን፡ የወንድማማች መዋደድ፡ የተልእኮ ዘመን ነው። ከታላላቅ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹን ልጥቀስላችሁ (ከዚያም ስማቸውን እዚህ ላይ እጽፍላችኋለሁ)፤ ጆን ዌስሊ፡ ጆርጅ ዋይትፊ-… ዋይትፊልድ፡ በ1739 ገደማ የነበረ ነው፡ ቻርለስ ጂ. ፊኒ፡ ድዋይት ሙዲ፡ እና ዊልያም ኬሪ፡ በ1773 ወደ ሕንድ የሄደው ታላቁ ሚሰዮናዊ ሰው። ዴቪድ ሊቪንግስቶን፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ። አያችሁ፡ እነዚያን ሁሉ፡ ከታላላቅ ሰዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በዚያ… በወንድማማች መዋደድ የኖሩ፡ የብዙዎቹ ስሞቻቸው ይዣለሁ፡ ይህም፡ ጥቁር ሰው፡ ነጭ ሰው፡ ቡናማው ሰው፡ ቢጫው ሰው፡ ሁሉም አይነት ግድግዳዎች ፈርሰዋል፡ እናም እነዚህ ሰዎች ወደ ተልእኮ መስክ የወጡ ናቸው። የወንድማማች መዋደድ፡ በየቦታው ላሉ ሕዝቦች ሁሉ እጁን ዘርግታ፡ መሄድ ወደሚችሉት ሁሉ ተከፍቶላቸዋል። ሌላ የተከፈተ በር ዘመን፡ ምክንያቱም… ከዚያ በፊት ያን ማድረግ አልቻሉም ነበር፡ መሄድ እስኪሳናቸው ድረስ ጳጳሱ እና—እና የሮም ጵጵሰና እና የመሳሰሉ ሁሉ ነገር ዘግቶባቸው

ነበር። በዚያ ዘመን ግን በሮች ተከፈቱ፡ ምክንያቱ "የተከፈተ በር" ዘመን በማለት አስቀድሞ ተናግሯልና።

58 በዚያ ዘመን ብዙ በሮችን ከፈቱ፡ የወንጌል በር፡ የተልእኮው መስክ በር፡ ወደ—ወደ—ክርስቶስ የሚመልስ በር፡ እና በዚያ ዘመን ሁሉም አይነት በር ተከፍቶ ነበር። ምን እንዳደረጉ ማየት ትችላላችሁ፡ እነዚያ ወንድሞች ታላቅ ስራ ሰርተዋል።

59 ከሰርዴስ ዘመን በኋላ ያለው ኮከብ፡ ከሰርዴስ ዘመን ካነቃቸው፡ ከጆን ዌስሊ በኋላ፡ (ከዚህ ጊዜ ወይም ፊት ከነበሩ ዘመናት ሁሉ በተለየ መልኩ) ላለፉት መቶ ሃምሳ ዓመታት ታላላቅ ሚስዮናውያን ምድርን ሁሉ ሸፍኗል። እስቲ አስቡት። ከሰማይ በታች ያለው ሕዝብ ሁሉ ቃሉን ሰምቷል። ብዙ፡ ብዙ፡ ብዙ ዓመታት ሸፍኗል፡ አያችሁ፡ ወንጌሉ ግን አይደለም፡ ቃል ብቻ ነው፡ "ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።" አያችሁ?

60 ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ባገለገልኩ ጊዜ፡ በዚያ ቀን መድረኩ ላይ፡ ሺ ጊዜ ሺዎች የሚቆጠሩ መሃመዳውያን፡ በዚያ ተቀምጠው ነበር። እና አንድ የመሐመዳውያን ሚስዮናዊ አገኘሁ። ይህ የመሐመዳውያን ሚሲዮናዊ፡ "ኦህ፡ ስለዚህች ውድ ነፍስ" ይል ነበር። እንግዲህ፡ ያ ሰው ለብዙ ዓመታት እና ለዓመታት በዚያ ቆይቷል፡ አንድ መሐመዳዊን ወደ ክርስቶስ ለውጧል። ምክንያቱም የመሐመዳውያን ሕጋቸው ከሜዶን-እና-ከፋርስ ስለ መጣ፡ እንደማይለወጥ ወይም እንደማይነካ ሕግ ነው፡ መሐመዳውያን ከሆኑ፡ ሁልጊዜ መሐመዳውያን ናቸው።

61 ስለዚህ እዚያ በደቡብ አፍሪካ ዋና ከተማ ፕሪቶሪያ ግቢ ቆሞ፡ ይህ ወንድም የሚለምንላት፡ አንዲት ነፍስ ነበረች። ቦታውም—ነጻ ክልል፡ ነጻ ክፈለ አገር በሚሉት፡ በኦሬንጅ ክፍለ አገር፡ እና በትራንስቫል ውስጥ ነበር።

62 ከዚያም ተጉዘን፡ እስከ ኬፕታውን እና ብሎምፎንቴን ወርደናል፡ ከዚያም አልፈን በመሄድ፡ በግራሃምስታውን፡ በምስራቅ ለንደን በኩል ተመለስን፡ ከዚያም ከ... ከኬፕታውን ከወጣን በኋላ ወደ ጆሃንስበርግ ተመለሰን፡ እና ወደ ባህር ዳርቻ ወጣን።

63 እና፡ መጨረሻው የገባንባት ከተማ ደርባን ነበረች፡ ብዙ ተወላጆች የሰበሰብንባት ከተማ ናት፡ አንድ መቶ ሃምሳ ወይም ሁለት መቶ ሺህ ተወላጆች ተሰብሰበው ነበር፡ መሐመዳውያን፡ ተወላጆች፡ በዙርያዋም... በዚያ... ከቸርችል ዳውን ይልቅ እጅግ በሚበልጥ... በ—ሩጫው ሜዳ ላይ፡ ብዙ ሳምንታት ቆየን፡ በዓለም ላይ ሁለተኛው ትልቁ ሜዳ ነው፡ አንደኛው ትልቁ የለንደን ነው፡ ከዚያ ደቡብ አፍሪካ፡ እና—እና ቸርችል ዳውንስ። የጎሳ ጦርነት ስለነበራቸው አጥር ተደርጎበት ነበር፡ ፖሊሶቹም (ሁለት ወይም ሶስት መቶ ጠባቂዎች) እርስ በርሳቸው እንዳይጣሉ፡ ትጥቃቸውን እያስፈቱ እያንዳንዱን ጎሳ ወደ ቅጥር ግቢ እያስገቧቸው ነበር፡ ጦሮቻቸው እና መውጊያዎቻቸውን ይዘው፡ ስፍራውን ሁሉ ሞልተው ነበርና። እዚያው መሬት ላይ ቁጭ ብለው፡ አንዱ አጥር አሻግሮ ሌላውን ጎሳ ይተያያል፡ የጎሳ ጦርነት። በዚያም አለቆቻቸውን፡ እና ንግስቶቹን... ተሸክመው... ትልልቅ ማራገቢያ የያዘ ሰው ያራግብባቸዋል። የሮዴዢያ ንግስት ሃያ-ሰባት መኪና ወይም የባቡር

ፉርጎዎች ሞልታ ከሮዴዥያ ድረስ ሰዎች ይዛ፡ ጉባኤውን ለመካፈል መጥታ ነበር። እና የ—የተለየ ባቡርም መጥቶ ነበር።

64 ጌታ ታላላቅ ነገሮችን፡ ድንቅ ተአምራትንና ምልክቶችን ያደርግ ነበር። ሌላስ ማን ነበር? የደርባን ከንቲባ፡ ሲድኒ ስሚዝ፡ ይየዛን ቀን ሰወጣ፡ "በአንገቱ ዙርያ፡ ትንሽ መለያ ያንጠለጠለ… ያ ሰው ምንድን ነው፡" ብዬ ጠየቅኩት? አንድ ጥቁር ሰው ነው፡ እዚህ አገር፡ ኔግሮ ብለን እንደምንጠራቸው። በዚያ የሰበኳቸው ሰውች እነሱን ነበር። ብዙዎቹ ምንም አይነት ልብስ አልነበራቸውም፡ ሴቶችም ወንዶቹም፡ አልለበሱም ነበር። ስለዚህ በእጁ ላይ፡ ጣዖት ይዞ ነበር በአንገቱ ላይም ትንሽ መለያ አንጠልጥሏል። "በአንገታቸው ላይ ያሉ መለያዎች… ምንድን ናቸው? " አልኩት፡

"ክርስቲያኖች ናቸው፡' አለኝ።

"ክርስቲያን? በእጁ ጣዖት ይዞ? " አልኩት፡

65 "ይኸውልህ፡ አየህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እሱ… ሶንግሃይ ነው፡" አለኝ፡ "ቋንቋቸው መናገር እችላለሁ፡" አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ "ወደሱ እንንዳና፡ ታናግረዋለህ፡ የፈለግከው ሰም ጥራው። ማንኛውንም ጥያቄ እንደምትጠይቀው ብቻ አናግረው፡ እኔም እጠይቀዋለሁ ከዚያም የተናገረውን መልሰህ እነግርሃለሁ።"

66 እኔም እንዲህ አልኩት፡ "እንዴት ነህ፡ ቶማስ? " ቶማስ ብዬ የጠራሁት ጥሩ ሰም ነው ብዬ ስላሰብኩ ነው። አልኩት—እንዲህ አልኩት፡ "እንዴት—እንዴት ነህ፡ ቶማስ? " እሱም አየኝ። እና "ክርሰትያን—ነህ፡" በማለት ጠየቅኩት?

"አዎን፡" ክ—ክርሰትያን ነበርና።

67 እኔም… ኦህ፡ እርግጥ ነው፡ አያውቀኝም። አይቶኝ አያውቅም… ማናቸውም ገና አላዩኝም አልኩት። እና "ያ ጣዖት ምን ይሰራልሃል፡" በማለት ጠየቅኩት?

እሱ፡ "ኦህ፡ አባቱ—አባቱ ያሰረለት ነው።" አያችሁ፡ አምላክ—ነው። አያችሁ?

68 እኔም "ያሰረልህ… አባትህ ነው፡" አልኩት። እና እንዲህ አልኩት፡ "ከሆነ፡ አንተ—ያንን ማንጠልጠል አይጠበቅብህም። አንተ'ኮ ክርሰትያን ነህ፡ አንተ ይህን ማንጠልጠል የለብህም።"

69 እሱም እንዲህ አለ፦ "እንግዲህ፡ አንድ ቀን አንበሳው አባቴን ተከትሎት መጣ፡ ትንሽ እሳትን አነደደና፡ ቃልቻው የነገረውን ጸሎት በዚህ ጣዖት ላይ አደረገ፡ ከዚያም ጣዖቱ አንበሳውን አባረረለት።" በዚያም ብዙ አውሬዎች ይገድሏቸዋል። እሱም…

70 እኔም እንዲህ አልኩት፡ "ይኸውልህ፡ ጠንቋዩ የነገረው ጸሎት—ሳይሆን፡ አንበሳውን ያባረረው እሳቱ ነው።" "አንበሳ እሳትን ይፈራል፡" አልኩት። እኔም "ቶማስ፡ አንተ እንደ ክርሰቲያን፡ ያንን አንተ ላይ ማንጠልጠል የለብህም። አንተ ከዚህ ጋር ምንም ህብረት የለህም፡" አልኩት።

71 እና እንዲህ አለ፡ "ኦህ፡ መልካም፡" እንዲህ አለ፡ "ምናልባት አሞያህ… " የማይታይ ኃይል፡ የማናየው አምላካችን ነው። **አሞያህ** ማለት የሆነ ነገር ነው፡ "እንደ ነፋሰ ያለ ኃይል።" እና "አሞያህ—ካልሆነላት፡ ይህ ይሆንላታል፡" አለኝ። ስለዚህ "አንደኛው ካልተሳካላት፡ በሌላኛው ለመጠቀም፡" ሁለቱን

ሸክፎ ይዟል። እንግዲህ፡ የክርስትና ጥንካሬው እዚህ ላይ ነው። ኸሃ-ሃም። አዎን። ኦህ፡ ማይ።

72 ነገር ግን በዚያ ቀን ከሰአት በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ በሩጫ መንገዱ በስብሰባ ላይ በወረደ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከፍቼ፡ እና የልብን ምስጢር መግለጥ ከጀመርኩ በኋላ…

73 አስራ አምስት ደቂቃ ብቻ የሚፈጅብኝን፡ አንድ ሰዓት ገደማ ፈጀ፡ ምክንያቱም አስራ አምስት የተለያዩ አስተርጓሚዎች ነበሩ። ስለዚህ እኔ—"ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፡" ካልኩኝ፡ **ይህ** ደግሞ "አህ፡ ባህ፡ ባህ፡ ባህ፡ ባህ፡" ይላል፡ **ይሄኛው** ይመጣና፡ "ግሉ፡ ግሉ፡ ግሉ፡ ግሉ"፡ ሌላውም **ቀጥሎ፡** "ኡም፡ ኡም፡ ኡም፡" እነደዚያው፡ ሁሉም ተርጓሚዎች "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ"፡ ማለታቸው ነው። እና እስኪያልፍ ድረስ ጠብቄ፡ የት እንደደረስኩ ስለሚጠፋብኝ፡ በመጨረሻ የተናገርኩትን መፃፍ አለብኝ።

74 ከዚያም ሲመለስ፡ "እንግዲህ፡ ሚስዮናዊያን ሊያድናችሁ ስለመጣው ኢየሱስ ነግረዋችኋል፡" አልኳቸው። ታውቃላችሁ፡ እነዚህ የተለያዩ ጎሳዎች፣ ከላይ እስከ ታች፡ ሲተያዩ ማየት ትችላላችሁ። እንዲህ አልኳቸው፡ "ሚስዮናውያን ይህን ነግረዋችኋል። ግን ያ ሚስዮናዊ… ይህንን መጽሐፍ ሲያነብላችሁ፡ እርሱ ታላቅ ፈዋሽ የሆነበትን አይታችኋልን ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ በሕዝብ መካከል ለዘላለም ይኖራል ብሎአልን? 'የማደርገውን ስራ እናንተም ታደርጋላችሁ።' እናንተ አንገታችሁ ላይ ካለው መለዮ ጋር፡ ክርስቶስን እንደ አዳኛችሁ የተቀበላችሁ ሁሉ፡ ኢየሱስ ዛሬ እዚህ ተመልሶ በሰዎች መካከል ሲራመድ ማየት ትፈልጋላችሁ እና በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ሲያደርግ ማየት ትፈልጋላችሁ? "

75 ኦህ፡ ሁሉም፡ "አዎን!" እያችሁ፡ ማየት ይፈልጋሉ። ያንን ያስፈልጋቸዋል።

76 እኔም እንዲህ አልኳቸው፡ "እንግዲያስ እሱ ይህን ካደረገ፡ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ እኛን ከተጠቀመ፡ ቃሉን ታምናላችሁ? "

"ኦህ፡ አዎን!" እያችሁ፡ መሐመዳውያን በዚያ ቁጭ ብለዋል።

77 በመድረክ ላይ የነበረች አንደኛ… ሁለተኛዋ ሰው መሐመዳዊት ሴት ነበረች። እና መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፡ ለሴቲቱ ራሴ፡ እንዲህ አልኳት፡ "እንግዲህ፡ እኔ እንደማላውቅሽ አንቺ ራስሽ ታውቂያለሽ፡ ቋንቋሽን እንኳ መናገር አልችልምና።" እሷም እውነት ነው ብላ ተስማማች።

78 እዚህ በዓይኖቿ መካከል ቀይ ነጥብ ነበራት፡ ይህ ማለት በመሀመዳውያን ውስጥ በደንብ የተዋበች ነበረች ማለት ነው። ስለዚህ፡ አልኳት፡ "እንግዲህ፡ አሁን፡ መፈወስ ከሆነ፡ እኔ ልፈውስሽ አልችልም።" ግን አልኳት፡ "ዛሬ ከሰዓት የተናገርኩት ነገር… መልእክቱ፡ ገብቶሻል? "

79 እሷም—ያንን መልሳ ከመሐመዳዊው አስተርጓሚ ጋር ተናገረች… እሷ ማንነቷ፡ ህንዳዊ ነበረች። እሷም "አዎን፡ ገብቶኛል። አዲስ ኪዳን እንብቤአለሁ፡" አለች። ኦህ፡ ነው። ኸሃ-እህም።

80 እያችሁ፡ እነሱም፡ በእግዚአብሔር ያምናሉ። እነሱም፡ የአምራሃም ዘር ናቸው። እያችሁ? እንዲህ አለች “በእግዚአብሔር አምናለሁ፡” ነገር ግን፡ “መሐመድ የሱ ነብይ እንደሆነ አምናለሁ” አለች። ኢየሱስ ልጁ እንደሆነ እናምናለን። እያችሁ? ሰለዚህ እንዳለችው፡ ኦህ፡ እሷ—እሷ “እግዚአብሔርን ታምናለች።”

81 እንዲህ አልኳት፡ “እንግዲህ ብሉይ ኪዳንን ካወቅሽ እና በአለፉት ሰዎች ውስጥ እግዚአብሔር ምን እንደ ነበረ ከተረዳሽ፡ እንግዲያውስ፡ ‘ክርስቶስ፡’ ብለን የምንጠራው ኢየሱስም፡ አምላክም-ነብይም ነበረ። እሱንም… ገደሉት። እናንተ ነጭ ፈረስ እየጋለበ ወጣ ሰለምትሉ፡ የገደሉት አይመስላችሁም። በካህናችሁ የተማራችሁት ያ ነው፡ እሱም፡ ‘ፈጽሞ እንዳልተገደለ፡ ነው። እና ከብዙ ዓመታት በኋላ፡ ሰርዓት ባለው ሞት ሞተ ትላላችሁ።’”

82 እንዲህ አልኳት፡ “ያን ታምኛለሽ። ይህ ኢየሱስ ግን፡ እንደ… በአዲስ ኪዳን መሰረት፡ ሞቶ ተነስቷል፡ መንፈሱንም ወደ ቤተክርስቲያኑ ላከው።” አሁን ከእናንተ ጋር ናቸው፡ እያችሁ። ያ መሃመዳዊ ቢሊ ግርሃምን የሞገተው ያንኑ ነው፡ እያችሁ። ተመሳሳይ ነገር፡ በተመሳሳይ መርህ።

83 እንዲህ አልኳት፡ “አሁን… መሐመድ የገባልሽ ቃል ከሌለ። ኢየሱስ ግን ቃል ገብቶልናል፡ ይህም እሱ የሚያደርጋቸው ነገሮች እኛም እንድናደርጋቸው ነው። አሁን፡ በቅዱስ ዮሐንስ 5፡19 ላይ የተናገረውን ታስታውሳላችሁ፡ ‘ከአብ ዘንድ ካላየሁ በቀር ከራሴ ምንም አላደርግም።’” እንዲህ አልኳት፡ “አሁን፡ ኢየሱስ መጥቶ ችግርሽ ምን እንደሆነ እና ለምን ወደዚህ እንደመጣሽ ካሳየኝ፡ ውጤቱ ምን እንደሆነ ከነገረሽ፡ ያለፍሽበት ህይወትሽን ከነገረሽ፡ የወደፊት ህይወትሽም ምን እንደሚመስል፡ የወደፊትሽ ምን እንደሆነ ቢነግርሽ… ያለፈውም ቢገልጽልሽ፡ በእርግጠኝነት ወደፊት ምን እንደምትሆኚ ታምኛለሽ።”

እሷ “እውነት ነው፡” አለች። እያችሁ፡ በአስተርጓሚው በኩል ነው።

እኔም “እሺ፡ ያድርግልሽ፡” አልኳት።

84 እና ታውቃላችሁ፡ መሐመዳውያን በሙሉ፡ ትኩር ብለው እያዩ ቆመዋል። መንፈስ ቅዱስም በተናገረ ጊዜ፡ “ባልሽ፡ ባለ ጥቁር ጺም፡ አጭር፡ ወፍራም ሰው ነው። ከሦስት ቀናት በፊት፡ ሐኪም ቤት ነበርሽ።” እንዲሁም፡ “ሁለት ልጆች አሉሽ። ይየሴቶች ምርመራ አደረገልሽ፡ እንዲህም አለሽ፡ ‘ማህጸንሽ ውስጥ እጢ አለ።’”

ወደ ታች ተመለከተች፡ አንገቷን ደፋች፡ “እውነት ነው፡” አለች።

85 እና እንዲህ አልኩ፡ “እንግዲህ፡ አዲስ ኪዳንን ካነበብሽ፡ ይህ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ በጉድጓድ አጠገብ እንደነገራት ሴት እንዲሁ ነውን? ”

“እውነት ነው።”

86 እኔም አልኳት፡ “እሺ፡ ወደ እኔ ወደ ክርስትያን ለምን መጣሽ? ለምን ወደ መሐመዳውያን ነቢይ አልሄድሽም? ”

እሷም “አንተ ልትረዳኝ ትችላለህ ብዬ ነው፡” አለችኝ።

87 እኔም አልኳት፡ “እኔ ልረዳሽ አልችልም። ነገር ግን አሁን እዚህ ያለውን ይህ ይህንን ኢየሱስን፡ ህይወትሽን የሚያውቅ እና ስለ አንቺ የሚያውቅ፡ ከተቀበልሽው ይረዳሻል።”

“ኢየሱስን እንደ አዳኜ ተቀብያለሁ፡” አለች።

88 አለቀ። ደቀደ። በዚያ ቀን ከሰአት በኋላ አሥር ሺህ መሐመዳውያን ወደ ክርስቶስ መጡ። አያችሁ? ወደ ሠላሳ ዓመታት ያህል በሚሰዮን መስክ ላይ፡ በሥነ ጽሑፍ አንድ ሰው ብቻ ተለወጠ፡ ወንጌል ሲገለጥ ግን፡ በአምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ፡ አሥር ሺህ መጡ።

89 እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናትን እንድንሠራ፡ ትምህርት ቤቶችንም እንድንሠራ አልነገረንም። ሁሉም መልካም ናቸው። ሆስፒታሎች እና ሌሎችም፡ እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገን ያውቃል፡ ፕሮግራሙ ነው፡ የቤተክርስቲያን ተልእኮ ግን “ወንጌልን መስበክ ነው!” እኛ ግን ትራክቶችን፡ ከአሰበሪ የወጡ ስነ ጽሑፎች እነበትናለን፡ እዚህ ቅርብ ያለ ቦታ ነው... እግዚአብሔር ይባርካቸው እነዚያ ሰዎች፡ እዚህ በዊልሞር፡ ኬንታኪ፡ ያለ ትኻሽ የሜቶዲስት ኮሌጅ ከምርጦቹ አንዱ ነው፡ በዚህ ጊዜ፡ በዓለም ካሉ ትንንሽ ቦታዎች፡ መንፈሳዊ ስፍራ እንደሆነ፡ እገምታለሁ። ጥሩ ሰዎች ናቸው።

90 እና ከአንድ ቦታ እየወጣሁ ነበር... ረሳሁት... ሮዴሺያ ነው፡ ከተማው ማን እንደሚባል አላውቅም። ቢሊ፡ ታስታውሰዋለህ? [ወንድም ቢሊ ፖል ተናገረ፡ “ሳሊስበሪ።”—አርታዒ።] አዎን፡ ሳሊስበሪ፡ ኒው ሳሊስበሪ። ሜሞሪዬ እሱ ነው። ኒው ሳሊስበሪ፡ ሮዴሺያ። እና ከሮዴሺያ እየወረድን ነበር እና አውሮፕላን ስንሳፈር የአሜሪካ ፓስፖርት የያዙ አየሁ፡ አንድ ወንድ እና ሦስት ሴት ልጆች። እንዲህ አልኳቸው፡ ወደ እነርሱ ጠጋ ብዬ፡ “ሰላም ናችሁ፡” አልኳቸው። “የአሜሪካ ፓስፖርት ይዛችሁ አይቼ ነው፡” አልኳቸው።

አንደኛው “እንግሊዘኛ ትናገራለህ፡” አለኝ።

እኔም አልኩት፡ “አዎን፡” “እ—አሜሪካዊ ነኝ፡” አልኩት።

“አይ፡ በጣም ጥሩ ነው፡” አለኝ።

ጠየቅኳቸው፡ “እየተጓዛችሁ ነው? ”

“አይ፡ እኛ ሚሰዮናውያን ነን፡” አለኝ።

“ኦህ፡ በጣም ደስ ይላል!” አልኩት፡ “በእውነት ስላገኘኋችሁ ደስ ብሎኛል፡” አልኩት። እና ጠየቅኩት “ከየት ናችሁ? የትኛው ቤተ ክርስቲያን ናችሁ፡ ወይስ በድርጅት ናችሁ፡ ወይስ ነፃ? ”

“አይ፡ ሜቶዲስት ነን። ከዊልሞር፡ ኬንታኪ ነን፡” አለኝ።

እኔም፡ “ጎሮዬ አጠገብ ናችሁ፡ ቤቴ በለው።” አልኩት...

እሱም እንዲ አለኝ፡ “ብቻ ወንድም ብራንሃም አንተ እንዳትሆን? ”

91 “አዎን፡ ጌታዬ። ልክ ነህ፡” አልኩት። አያችሁ፡ ያም—ነገር ወዲያው ዝም አሰባለው። ከዚያ በላይ መናገር አልቻለም። እና ከዚያ በኋላ እንቅስቃሴውን—አስተዋልኩት፡ ወደ ሴቶቹ አየ፡ **እንዲህ** እርስ በእርሳቸው ተያዩ። “ስማኝ እስኪ፡ ልጄ፡” አልኩት። ገና ልጅ እግር ነው። እና ሴቶቹም እንዲሁ... ጠየቅኳቸው። እና እንዲህ አልኳቸው፡ “እስኪ እንደ ክርስቲያኖች

በመሠረታዊ መርሆች ላይ ለአንድ ደቂቃ ብቻ ላናግራችሁ፡ ሁላችንም፡ እዚህ ያለነው ለተመሳሳይ ታላቅ ዓላማ ነው። እናንተ ሶስት ሴቶች እና አንተን ወጣት ልጠይቃችሁ፡ 'እንደው በጌታ በኢየሱስ ስም... ' እዚህ ሁለት ዓመት እንደቆያችሁ ተናግረሃል። 'አሸንፈህ ወደ ጌታ ያመጣኸው አንድ ነፍስ ላይ ጣትህን መጠቆም ትችላለህ? አንዲት ነፍስ?'" ሁሉም አልቻሉም። አንዲት ነፍስ የለም።

92 "ስሜታችሁን መጉዳት፡ በጭራሽ አልፈልግም፡" አልኳቸው። እና ኣንዲህ አልኳቸው፡ "እዚህ የምታደርጉትን ነገር አደንቃለሁ፡ እናንተ ልጃገረዶች ግን በእናታችሁ ቤት ሣህኖቿ ላይ ብታግዟት ይሻላችኋል። እውነቴን ነው። እዚህ ምንም ስራ የላችሁም። ይህ እውነት ነው።"

93 መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ የኃይሉ ችሎት እየውገለጠ በማሳየት የሚሰብክ ካልሆነ በቀር ማንም ወደ መስክ ቢወጣ ሥራ የለውም፡ ምክንያቱ እነዚህ ሰዎች—ሊነካ የሚችል ብቸኛው ነገር ይህ ነው። አሁን ምን አይነት አመፆች እንደተነሱ ተመልከቱ፡ እውነተኛው ወንጌል ስላልተሰበከላቸው ነው። በቃላት መልክ ተሰጥቷቸዋል። እንግዲህ፡ ያ ምን እንደሆነ አያችሁ? ያማ የሉተር ዘመን የነ—የነ "ያመለጡ" ቅጥያ ነው፡ ለዓለም በነፃ ህትመት የተበረከተበት፡ መጽሐፍ ቅዱስ በነጻ የተሰጠበት ነው፡ በትክክል።

94 እንግዲህ፡ አሁን በቀጥታ፡ ወደ ታላቁ ዘመን እንግባ። አሁን፡ እስኪ እንጀምረው፡ ይመስለኛል... 7ኛው ቁጥር፡ ስላምያው ላይ ደርሰናል። በ...

> ... ወደ... **ፊላዴልፊያ እንዲህ ጻፍ፡ የዳዊት** መክፈቻ ያለው፡ **ቅዱስና እውነተኛም የሆነ እርሱ፡ እንዲህ ይላል፡** የሚከፍት፡ **የሚዘጋም የሌለ፡ የሚዘጋ፡** የሚከፍትም **የሌለ፡**

95 ድንቅ ንግግር ነው! አይደል? በአንድ ደቂቃ ውስጥ እ—እመለስበታለሁ፡ ምክንያቱ በሚቀጥለው ቃል ላይ በተሻለ—ይብራራልና።

> **ሥራህን አውቃለሁ፡ እነሆ፡ በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ፡ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፡ ኃይልህ ምንም ትንሽ** ቢሆን፡ **ቃሌን ጠብቀሃል**ና፡ **ስሜንም አልካድህምና።**

96 እንግዲህ፡ አሁን ተመልከቱ—ምድሪቱን ካጥለቀለቀው፡ ከወንድማማቾች መዋደድ ታላቁ የሚስዮናውያን እንቅስቃሴ በኋላ፡ እነሆ የነበራቸውን የሚወሰድባቸው፡ ሌላ ዘመን መጣ። ወደ ተለያዩ ክፍሎች ዓለም ስላሰራጩት፡ ስለ ሰነ ጽሑፋቸው፡ እና ሰለ ሌላ ነገራቸው፡ የምቃወመው ነገር የለኝም። አሁን፡ የኃይማኖት ተቋም የሆነችው ቤተክርስቲያንም እንደገና ወደ ትምህርት ቤት ሥራ ተመልሳለች። አያችሁ፡ ወደኋላ ተመልሳለች።

97 ታላቁ የኃይማኖይት ተቋም ከተቋቋመ በኋላ፡ ኢየሱስ "የተከፈተውን በር" አዘጋጀ። የዌስሊያን ዘመን ከገባ እና የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ስር ሰድዳ፡ እያደገች፡ ከተመሰረተች በኋላ፡ በአሁኑ ጊዜ ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል፡ ከታላላቅ አንዷ የሆነችውን፡ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ከሆነች በኋላ፡ እና ያን ጊዜ፡ ያኔ የተከናወነው ነገር፡ ይህ ነበር፡ ወደ ሎዶቅያ ዘመን ገና ሳይገቡ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን "የተከፈተ በር" አሰናዳ።

98 ይህን በዚህ መልኩ የምልበት ምክንያት፡ መደራረብ ምን ማለት እንደሆነ እንድታዩት ነው። አያችሁ? ከሚሰዮናዊ በር ዘመን ዘንድ ነው። አያችሁ፡ ነገር ግን፡ የዳዊት መክፈቻ—እና የመሳሰሉትን ነገሮች እንዳሉት ነግሯቸው ነበር። እዚህ ግን ከሚሰዮናውያን ዘመን በኋላ አሁን በቤተ ክርስቲያኒቱ ፊት፡ ያስናዳላቸው ነገር እንዳለ ይናገራል፡ እና እነ ዋይትፊልድ፡ እና—እና ሌሎች ሁሉ፡ እነ ፊኒ፡ እና ሳንኪ፡ እስከ ሙዲ ድረስ (ሙዲ ከመጨረሻዎቹ አንዱ ነው።) በቤተክርስቲያኑ ፊት የተከፈተ በር እስከ አሁን ድረስ ይደርሳል። ኦህ፡ አሁን ማየት ያለባችሁ እዚህ ላይ ነው። በፊላደልፊያ እና በሎዶቅያ ዘመን መደራረብ፡ መካከል ነው።

99 ኢየሱስ በር ነው! አሁን፡ ከእኔ ጋር ዮሐንስ 10፡17 ላይ ክፈቱ። አሁን ይህን እናጠናክረው፡ ብዙዎቻችሁ እንደምታምኑ... እርግጠኞች ሁኑ። እስኪ እንዲህ የሚል ሰው ካለ፡ “እንግዲህ፡ ይህ—ፈጽሞ ከእኔ አይደለም... ራሱ የተናገረው ነው።” ብቻ እኔ አነበዋለሁ። ዮሐንስ፡ 10ኛው ምዕራፍ፡ ቁጥር 17። ዮሐንስ 10፡ 17። መልካም፡ እነዚህ ቃላት እናንብብ። ይቅርታ አርጉልኝ፡ ዮሐንስ 10፡7 ነው፡ 17 አይደለም።

> **ኢየሱስም አላቸው... እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ እኔ** የበግ በረት **በር ነኝ።**

100 ይህ ወደ በረከት መግቢያ ነው። ወደ ክርስቶስ እንዴት እንገባለን? እሱ ምንድነው? የበግ በረት። ብዙ ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ “ምንድን? ሰው ሆኖ፡ በር ሊሆን ይችላል፡” አሰብ ነበር? እና፡ በዚያ—ወደ ምስራቃዊ አገሮች፡ በዚያ አንድ ቀን ያየሁት አስተዋልኩት እና እረኛው፡ ሲመሽ፡ በጎቹን በሙሉ ወደ ጉሮኖ ይወስዳቸዋል፡ በበር በኩል ያስገባቸዋል። ሁሉንም ካስገባቸው በኋላ፡ መግባታቸውን ለማየት ሁሉንም ይቆጥራቸዋል። ከዚያም፡ ራሱ ደግሞ በሩ ላይ ይተኛል። እሱን ሳይሻገር፡ ወደ በጎች ሊገባ የሚችል፡ ወይም ከበጎቹም ወደ ውጭ ሊወጣ የሚችል ማንም አይኖርም። እንግዲያውስ፡ ኢየሱስም የበጎች በረት በር፡ እሱ ነው።

101 እና በትንሽ ብሪቲሽ ጂፕ ውስጥ ተሳፍሬ ነበር፡ እና ለባልደረባዬን፡ እንዲህ አልኩት፡ “እነዚያ... ” እረኞች ከተማው ውስጥ መጡ፡ እና ጥሩምባ ተነፉ፡ እና ሁሉም ሰው ፍሬኑን ያዘ፡ እናም “ምን ተፈጠረ? ” ብዬ አሰብኩ፡ በከተማይቱም በጎቹን ይዞ የሚያልፍ እረኛ ስለ ነበረ ነው።

102 እንግዲህ፡ ወደ ምስራቅ ላይ፡ እንደዚህ አይደለም። ምርቶቻቸውን በሙሉ—በገበያ አጠገብ ባሉ ቤቶች ጎን ላይ ይዘረጋሉ። ፖምና ፒር፡ እና ልዩ ልዩ አይነት ፍራፍሬዎች፡ እና ወይኖች እንዲሁ በሚያምር ሁኔታ ይደረደራሉ፡ እንደዚህ ባለው መደርደሪያ ላይ ተደርድርው፡ እንደ ዘለላ ይወርዳሉ። እና ሻጮቹ ሁሉ ቆመው ፍራፍሬዎቻቸውን እና ያላቸውን ነገሮችን እንድትገዟቸው ሊጎትቷችሁ ይሞክራሉ።

103 እንግዲህ፡ እረኛው፡ የጀመረው በዋናው መንገድ ነው። እኔም “ወንድሜ፡ ጫጫታው ያለው ብዚህ በኩል ነው፡ ይሄን እማ ቆሜ አየዋለሁ፡” አልኩት።

104 እና ከእኔ ጋር የነበረው ወንድም “ወንድም ብራንሃም፡ ተመልከት። ትገረማለህ፡” አለኝ። ሁሉም ነገር ቆሟል። እረኛው ለሌላ ምንም ትኩረት ሳይሰጥ፡ ይሄዳል፡ በጎቹ ሁሉ እሱን ይከተላሉ። በትክክል ይከተሉታል! እረኛው

እንዲህ ዞሮ ከተመለሰ፡ ከኋላው... ያለው በግ እንዲሁ ዞሮ ይመለሳል፡ ቀጣዩም እንዲሁ ይከተለዋል፡ ከሱ በኋላ ያለውም እሱን ይከተላል፡ እንዲሁ እየተከታተሉ ያንን ዙር ይዞራሉ።

105 ኦህ፡ እኛም እረኛውን የምንከተለው በዚህ መንገድ ነው! ትክክል። ማዶ ጫፍ ላይ የሆነ ነገር ለማግኘት ጎዳናው መኃል ቆርጠው ይሻገራሉ፡ በጎቹም ልክ እንደ ውሻ ይከተሉታል። በዙርያቸው ላይ ፍራፍሬዎች ያያሉ፡ ነገር ግን እረኛውን ተከትለው ይሄዳሉ። አቤት፡ እንዴት ደስ ይላል! አያችሁ፡ “ኦህ፡ ወንድሜ፡ አሁን የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ብሆን ኖሮ፡ አሁኑኑ በሰበክኩ ነበር፡” አልኩት። ይኸው ነው። አዎና፡ ወደ ቀኝ—ወደ ግራ ሳይሉ፡ እረኛውን ብቻ ይከተሉታል።

106 ቤተክርስቲያንም እረኛውን ተከተላ፡ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራን መንፈስ ቅዱስን በመከተል፡ እስከመጨረሻው ያደረገችው ይህንኑ ነው፡ ይህ በአበቦች ያጌጠ ቤተ ክርቲያን ነው፡ ያም ብዙ ዶክተሮች ያሉበት እነ **እከሌ-እና-እከሌ** ወይም **እከሌ-እከሌ** ያሉበት ነው ሳትል፡ እረኛውን ብቻ ተከተለች። እረኛው በሄደበት ሁሉ፡ በጎቹ ይከተሉታል፡ “በጎቼ ድምፄን ያውቃሉ፡ እንግዳንም አይከተሉም።” በትክክል። እረኛው... በጎቹን ሊያንቀሳቅሷቸው የሚችሉትን ድምጾች በሙሉ ያውቃቸዋል።

107 ከዚያም ከከተማው እንደወጣን፡ በጣም የሚገርም ነገር አየን፡ እና ግጦሽ—እየሁ ሰዎችም እዚህና እዚያ ነበሩ፡ አህዮች፡ እና ላሞች፡ አሳማዎችም ነበሯቸው፡ በጎችም፡ ፍየሎችም፡ እና ሌሎችም በዚያ ነበሩ። እኔም “መልካም፡ እነዚያስ ሰዎች ምንድን ናቸው፡” ብዬ ጠየቅኩት?

“እረኞች ናቸው፡” አለኝ።

“አህዮችን የሚጠብቅ እረኛ፡” ብዬ ጠየቅኩት?

“አዎን፡ ጌታዬ፡” አለኝ።

እንዴ፡ እኔ’ኮ “እረኛ ሲባል ለበግ—ይመስለኝ ነበር፡” አልኩት።

108 እርሱም፡ “አይ። **እረኛ’ማ** ‘አጋች፡ አስጋጭ፡’ ነው አለኝ። እንደውም በእናንተ አገር ‘ካውቦይስ’ ወይም—እንደዚያ ነገር ይባላሉ።”

“ኦህ፡ ገባኝ፡ እረኛ ማለት አጋች ነው፡” አልኩት።

“አዎን።”

“መንጋዎቹ ላይ ተመለከተ።”

109 “ትክክል።” እንዲኢህ አለ፡ “የሚገርመው ነገር በመሸ ጊዜ ነው፡ እንደው... ይደንቃል። አንተም አገልጋይ ስለሆንክ፡ ይሄን ብነግርህ፡ መልካም ነው።” እንዲህ አለ፡ “እርግጥ ነው ሁሉንም ይጠብቃቸዋል... በቀን ውስጥ ይረዳቸዋል፡ መልካም ነገር እንዲያገኙ ይመራቸዋል ያግዛቸዋል አመሻሹ ላይ ግን ሌላ ነው። ማታ አመሻሽ ላይ ግን... በቅሎዎች እና አህዮች እና—ግመሎቹ፡ እና ያለውን—ሁሉ፡ መስኩ ላይ ይተዋቸዋል። በጎቹን ግን ሰብስቦ ወደ በረት ይወስዳቸዋል።”

110 “ኦህ፡” “ጌታ ሆይ፡ እንደፈለክ አርገኝ፡ በግ ብቻ ልሁን!” አልኩኝ፡ አያችሁ? ሌሊቱ ሲመጣ፡ ወደ በጎች በረት መግባት እፈልጋለሁና። በበሩ በኩል መግባት፡ በበሩ መምጣት እፈልጋለሁ። ዮሐንስ 17፡7 ላይ፡ ወይም—

ወይም “እኔ… ” አለ፡ ሳይሆን፡ 10፡7 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ “የበጎች በር እኔ ነኝ። ከእኔ በፊት የሚመጡት ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፡ በጎቹ ግን አልሰሙአቸውም። በሩ እኔ ነኝ፡ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፡ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።”

111 “አሁን፡ እኔ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ፊት፡ በፊላደልፊያ ዘመን እና በሎዶቅያ ዘመን መካከል፡ በተከፈተ በር ቆሜአለሁ።” ኦህ፡ አሁንስ ገባችሁ ወይ? ማሰቢያ ብሎኖቻችሁ በደንብ ጠበቅ አርጋችኋል? አሁን አድምጡኝ፡ ይህ ጥሩ ነው። አለት ውስጥ እንዳለ ማር ነው፡ እላችኋለሁ፡ እንቊዎቹን ይዛችሁ እስኪያበሩ ድረስ በደንብ ወልውሏቸው። “እኔ የበጎች በረት በር ነኝ!” አሁንስ፡ የተሰናዳው በር ምንድን ነው?

112 እስቲ በሃሳብ ወደ ኋላ እንመለስ። እናም ያ ታላቅ የሜቶዲስት ሚሰዮናዊ ዘመን፡ የመቀደስ መልእክት ይዞ አገሪቱን አጥለቀለቀ። ሉተርም በጽድቅ። ዌስሊ የቅድስና መልእክት ይዞ መጣ። በሜቶዲስት ዘመን መጨረሻ ላይ፡ ፍጻሜ ላይ፡ ስር መሰደድ ሲጀምር ታላቅ ድርጅት መሆን ጀመረ። ማንኛውም ቤተ ክርቲያንም…

113 አሁን አድምጡኝ፡ ጠንከር ይላልና። በየትኛውም በታሪክ ቃርሚያ ውስጥ እንዲያሳየኝ ማንም ሰው ልጠይቅ። ያለ ምንም ድርጅታዊነት፡ እግዚአብሔር በጴንጤቆስጤ መንገድ ያስነሳት የትኛይቱ ቤተ ክርስቲያን፡ ልክ እንደተደራጀች፡ ትሞታለች እንደገናም ህይወት አትዘራም። አዎን፡ አባልነት ይቀጥላል፡ ሪቫይቫል ግን በጭራሽ አይሆንላቸውም። የሉተር ሪቫይቫል ህይወት አልዘራም፡ የሜቶዲስት ሪቫይቫል ህይወት አልዘራም፡ የጴንጤቆስጤው ሪቫይቫልም በጭራሽ ህይወት አይዘራም። የለም፡ ወዳጄ። ተደራጅተዋልና፡ እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሲናገር፡ የኒቆላውያን አስተምህሮ “እጠላዋለሁ፡” ብሏል።

114 አሁን፡ ልብ በሉ፡ ማንንም እየተቃወምን አይደለም። ጥሩ ሰዎች በሁሉ አሉ። የእግዚአብሔር በጎች በሁሉም ሰፍራዎች ይገኛሉ። እውነት ነው። ትክክል ነው። ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ምንም ቢሆኑም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም ከተወለዱ የእግዚአብሔር ህዝብ ናቸው። የእግዚአብሔር ህዝብ ናቸው፡ ድርጅቶቹ ግን አጣበቡባቸው። ከሜቶዲስት ወደ ባፕቲስት ከዚያም ወደ ካምቤልላይት እና የታሸጉ ፊደሎች፡ እና ሌሎችም፡ ፊደሎች ለብሰው—ከቦታ ወደ ቦታ እያሸጉዋቸው ቆይቷል።

115 መልካም፡ ጌታ በዚያች ዘመን መጨረሻ፡ የተናገረው ምንድነው፡ “የበጎች በር እኔ ነኝ።” እስኪ፡ በእነዚህ ሁለት ዘመናት መካከል፡ ስለ ኢየሱስ የተከፈተው በር ምንድነው? በ1906፡ የሜቶዲስት ዘመን እና—እነ—ድዋይት ሙዲ እና ሌሎች ከሰፍራው ደብዝዘው ሊወጡ ሲሉ፡ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስን የሚሞሉበት መለቀቅ ተወለደ፡ በልሳኖች መናገር እና ሌሎች ነገሮች ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመለሱ። ያ ልክ በ፡ በ 1906፡ ገደማ ነው።

116 እንግዲህ፡ ያኔ ምን ሆነ? ከዚያ በኋላ ታውቃላችሁ፡ በመጀመሪያ የሆነው ነገር፡ የቀድሞውን ጠቅላይ ጉባኤ ማደራጀት ጀመሩ፡ አሁን አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ በመባል ይታወቃል። አያችሁ፡ ከዚያ ቤተ ክርስቲያን ያ ተደራቢ ነው። ከዚያስ ምን ሆነ? የተከፈተ በር አሰናዳ፡ “የተከፈተ በር።”

117 አሁን እስቲ እናንብበው፡ ልክ እንደተጻፈው ቃል በቃል ያዙልኝ። አያችሁ፡ “እነሆ… ” እስኪ እንየው፦

**… የሚዘጋም የሌለ፡…**

**… በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ፡…**

118 በሌላ በኩል ነው፡

**ሥራህን አውቃለሁ፡ እነሆ፡ በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ፡ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፡…**

119 “የተከፈተ በር።” እሱ ምንድነው? የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይ አምላክነት መገለጥ ነው፡ የሥላሴ ሁለተኛ አካል ሳይሆን፡ እግዚአብሔር ራሱ ሥጋን ሆነ በእኛም ዘንድ አደረ። መገለጡ…

120 አሁን፡ ልብ ካላችሁ፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ ትንሽ ማንበብ እንቀጥላለን።

**… የሚዘጋውም፡… ኃይልህ ትንሽ** ቢሆን፡… **ቃሌን ሰሜንም** አል**ካድህምና።**

121 **በዚህ** ኋላኛው ዘመን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ስሙ ሲነገር፡ ስሙ ጠፍቷል፡ ሉተርም ህያው እንደመሆኑ ስም ይዞ ወጣ፡ እና **ሞተዋል** (ትክክል ነው?) “አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ።” **እዚህ** በእነዚህ ሁለት ዘመናት መካከል፡ የኢየሱስ ስም እንደገና መጣ። “በተከፈተው በር፡” መካከል። እንግዲህ፡ ማን ስለመሆኑ፡ መገለጥ ነው፡ እርሱም አምላክነቱ፡ የአምላክነቱ መገለጥ ነው።

122 እንግዲህ፡ ይህ በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ራሱ የገለጠው ነው። እንግዲህ ተመልከቱ፡ ዮሐንስ ቆሞ ሲያየው፡ ሰባቱን የወርቅ መቅረዞች መካከል፡ እጁን ዘርግቶ ቆሞ ነበር። አንደኛው መቅረዝ ይኸውና፡ ሁለተኛ፡ ሦስተኛው፡ አራተኛው፡ አምስተኛ፡ ስድስተኛ፡ ሰባተኛ፡ እጆቹንም በመስቀል ቅርጽ አውጥቶ። “እኔ አልፋና ኦሜጋ ነኝ፡” ይላል። በሌላ አነጋገር፡ “በመጀመሪያ የበላይ እሆናለሁ፡ በመጨረሻው የበላይ እሆናለሁ።” ብርሃናት በምስራቅ ይወጣሉ ወደ ምዕራብ ይጠልቃሉና። በጣም አሳፋሪ፡ ጨለማ ጊዜ ነበር፡ “ሲመሽ ግን ብርሃን ይሆናል።” **እዚህጋ** በምሰራቅ በአንድ በኩል የወጣው ያው የወንጌል ሃይል፡ አሁን በሌላ በኩል በምዕራቡ ዓለም አበራ፡ “አልፋ እና ኦሜጋ፡ እኔ ሀ ነኝ እና እኔ ፐ ነኝ።” በእጆቹ! ገባችሁ?

123 አሁን፡ በራእይ ምዕራፍ 1 ላይ ምን አደረገ? የበላይ አምላክ መሆኑን ለመጀመሪያው ቤተ ክርስትያን፡ ለኤፌሶን ገለጠ። ትክክል ነው? እንግዲህ፡ አሁን ልብ በሉ። በሚከተሉት በእነዚህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት፡ በአምላክነቱ ራሱን የገለጠው በክብሩ መልክ ብቻ ነው፡ ነገር ግን በዚህ በመጨረሻው ላይ፡ ወደ መጀመሪያው መጀመሪያ ተመልሶ ፐ ሆነ። አያችሁ፡ “የመጀመሪያ እና የመጨረሻ።” “እኔ ፊተኛውና መጨረሻው ነኝ፡” ብሏልና፡ ፊተኛው ዘመን፡ አሁን የመጨረሻው ዘመን ነው። እና…

124 እናንተ ግን እንዲህ ትላላችሁ፡ “እሺ፡ ያ እንዴት ሊሆን ቻለ? ያንን ያወጣው ማን ነው?” መገለጥ ነበር! እዚህ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ ተቀብላችችሁታል፡ ምክንያቱም የእርሱ-… አሁን አንድ ነገር ልናገር ነው። ተመልከቱ! የገዛ ቤተክርስቲያኑ በሙሉ በራሱ መለኮታዊ መገለጦች ላይ የተመሰረተች ናት።

ልክ ነው ወይ? ይህን ካላመናችሁ፡ ሁላችንም ማቴዎስ 16፡18 እንክፈት፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መገለጥ ሁሉ በሙላት በማንነቱ ዙርያ የተገነባ መሆኑ ታውቃላችሁ። መላ ቤተክርስቲያኑ የትገነባችው በማንነቱ ዙርያ ባለው መገለጥ ላይ ነው። አሁን፡ በዚህ እንጀምር… በ14ኛው ቁጥር አካባቢ… እንጀምራለን፡

እና **እንዳንዶች እንደሚሉት… አንዳንዶች፡ መጥምቁ ዮሃንስ ይሉሃል፡…**

ጥያቄ—ው የነበረ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡

… በ**ፊልጶስ ቂሣርያ ዳርቻ ላይ፡ ሰዎች፡ እኔ የሰው ልጅ… ማን ነው ይሉኛል? ብሎ፡ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው።**

ቁጥር 13 ላይ፡ ምዕራፍ 16፡13 ላይ።

**እነርሱም እንዲህ አሉት፡…**

125 አሁን ተመልከቱ፡ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የተናገራት ሰፍራ እዚህ ጋር ነው፡ ይህም… የመገለጥ መጨረሻው ነው።

**አንዳንዶች፡ መጥምቁ ዮሐንስ ነው… ይላሉ፡ ሌሎችም፡ ኤልያስ፡ ሌሎችም፡ ኤርምያስ፡** እና ሌሎችም… ከ—ከ… **ወይም ከነቢያት አንዱ ነው።**

እርሱም **ሁሉንም—ሁሉንም** አላቸው (ሁሉንም፡ በአንድነት)፡ **እናንተስ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ?**

**ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡ አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።** (ኦህ፡ ማይ!)

**ኢየሱስም መልሶ፡ የዮና-ልጅ ስምዖን—ስምዖን ሆይ፡ ብጹዕ ነህ፡… በሰማያት ያለው አባቴ** እንጂ፡ **ሥጋና ደም** ይህን **አልገለጠልህም።**

126 ኦህ፡ ማይ! "ይሄን ፈጽመህ ከትምህርት ቤት አልተማርከውም። ይህን የምታውቁበት ሌላ መንገድ ሊኖር አይችልም፡ የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ፡ እኔ እርሱ እንደሆንኩ ያወቅህበት ብቸኛው መንገድ፡ ከሰማይ በተገለጠልህ መንፈሳዊ መገለጥ ብቻ ነው።" ኢየሱስም፡ "እኔ እርሱ እንደሆንኩ ባታምኑ፡ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ። እኔ እሱ ነኝ!"

**… እኔም… እልሃለሁ፡… አንተ ጴጥሮስ ነህ፡… በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም** አይ**ችሏትም።**

127 ምንድነው? መንፈሳዊ! መንፈሳዊ! መንፈሳዊ እውነት! የጌታ ቃል!

128 እንግዲህ፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን በሰጠው በዚህ ታላቅ መገለጥ፡ ይህም እግዚአብሔር ልኮ በሁለቱ ዘመናት **መካከል** ለራሱ የገለጠው "የተከፈተ በር" ነው። በሎዶቅያ ዘመን—አልነበረም፡ ወይም **በዚህ** በሌላ ዘመን (በፊላደልፊያ ዘመን) ውስጥ አልነበረም፡ ነገር ግን በመካከል (በመደረብ) ላይ ነበረ ምክንያቱ… ትንሽ ዝቅ ብዬ አረጋግጥላችኋለሁ፡ ያኔ ይገባችኋል፡ እያችሁ። ይሄን ማየት

ከፈለጋችሁ፡ አለማየት እስከማትችሉ ድረስ፡ በደንብ አጠናክረዋለሁ፡ አያችሁ። በጣም ጥሩ።

129 አሁን፡ ቤተ ክርስትያኑ የተገነባችው እርሱ ማን በመሆኑ መገለጥ ላይ ነው። እንግዲህ፡ ይህ እውነት እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? ቤተ ክርስትያኑ እርሱ ማን በመሆኑ መገለጥ ላይ ሰራት። እሺ፡ አሁን ምን አለ? "ማንም የማይዘጋው!"

**ሥራህን አውቃለሁ፡ እነሆ፡ በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ፡...**

130 "የተከፈተ በር" ምንድነው? የኢየሱስ ክርስቶስ ልዑል አምላክነት መገለጥ! **በዚህ** ዘመን፡ በዚህ ዘመን ለመጀመሪያ ለቤተክርስቲያኑ ምን አላት? እንዲህ አለ፡ "የነበረው፡ ያለው፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ! መጀመሪያው እና መጨረሻው እኔ ነኝ! ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ!" **እዚህ** ለመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ራሱን አምላክነት አድርጎ፡ ሦስት ጊዜ ተናገራት፡ ወደ መጨረሻው የቤተክርስቲያን ዘመን ከመግባቱ በፊት፡ እንዲህ አለ፡ "እነሆ በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ።" መገለጡን ማየት ከፈለጋችሁ፡ ቤተክርስቲያኑን የሚገነባበት፡ ይኸው ይህ ነው። እና ቤተክርስቲያኑን የሚወስድበት ብቸኛው መንገድ፡ ወደ እርሱ ምንነት መገለጥ ነው። በእውነት!

131 ተመልከቱ! አብርሃም ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ፡ ወይም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ፡ በዚያ ቀን፡ "እኔ አርጅቻለሁና፡ እነዚህ ነገሮች እንዴት ይሆናሉ? እና ብቸኛው ወራሼ—ይህ ባርያዬ የደማስቆ ሰው፡ ኤሊዔዘር ነው አለ።" እንዲህ አለ፡ "እኔ አርጅቻለሁ፡ አንተም ልጅ እሰጥሃለሁ ብለህ ቃል ገባህልኝ። እንዴት ታደርገዋለህ? እንዴት ይሆናል? "

132 እና በሰው ሁሉ ላይ እንደሚወድቅ ከባድ እንቅልፍ፡ ሞት፡ እንደወደቀበት ልብ በሉ። እና እንዲህ አስተዋለ፡ ሐጢአተኛ ሁሉ ወደ ሲኦል መውረድ ይገባዋልና፡ ከመወሰዱ በፊት የሚጨስ ምድጃ መጣ። እንስሳ (ጊደርን) አርደዋል፡ በግ እና ሴት ፍየል፡ እርግብ እና ዋኖስን አርዶ ነበር። ዋኖሱንና ርግቧን ፈጽሞ ለሁለት አልከፈለውም። ከዚያም ይህ ትንሽ ነጭ ብርሃን ወደዚያ ወረደ፡ እና ለሁለት ተከፍለው በተቀመጡ እንስሶች መካከል ወዲያና ወዲህ ተመላለሰ፡ ይህም ከአብርሃም ጋር ያለውን ቃል ኪዳን የሚያረጋግጥ ነበር።

133 አሁን፡ በጃፓን ውስጥ፡ እዚህ ጃፓናዊ ሰው ካለ፡ በጃፓን እንዴት ቃል ኪዳን እንደሚገቡ ታውቃላችሁ? እርስ በእርሳቸው ጨው ይጣጣላሉ። ትንሽ የጨው ጣሳ ይዘው፡ ይቀመጣሉ፡ ይነጋገራሉ፡ "**እንዲህ-እና-እንዲያ** ታደርጋለህን? " "አዎን፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** አደርጋለሁ።" ከዚያም ቃል ኪዳን ገብተው ጨው ወስደው በአንዳቸው ላይ ይጣጣላሉ፡ ምክንያቱ ጨው ነገሮች እንዳይበሰብሱ ጠባቂ ነውና፡ አያችሁ። መልካም፡ እርስ በእርሳቸው ጨው ይጣጣላሉ፡ ያም ቃል ኪዳን ነው።

134 አሜሪካ ውስጥ፡ ቃል ኪዳን ስንገባ፡ እንዲህ እንላለን፡ "መልካም፡ ይህ እና ያ ነገር ታደርጋለህን? " "ይህ እና ያ ነገር አደርጋለሁ።" መጀመሪያ የምናደርገው ነገር ታውቃላችሁ፡ "እንጨባበጣለን!" እጃችንን እንጨባበጥበታለን፡ ያም ቃልኪዳን ነው።

135 በምስራቃውያን ዘንድ፡ ቃል ኪዳን የሚገባቡበት መንገድ፡ ግን፡ አንድ ነገር ይጽፉሉ። በአብራሃም ዘመን፡ ውል ተጻጽፈው፡ እንስሳ ያርዳሉ። እንስሳውን አርደው እንዲህ ይከፍቱታል፡ በመካከልም ይቆማሉ፡ ውሉን ጽፈው **እንዲህ** ይቀዱታል። አንዱ አንድ ቁራጭ ይወሰዳል፡ ሌላውም ሁለተኛው ቁራጭ ይወስዳል። ከዚያም "ይህን ውል ካልጠበቁ ሥጋቸው እንደ ሞተው እንስሳ ይሁን" ብለው ይምላሉ። እና አሁን ይህ ውል መቼም ሊጸና የሚችለው ብቸኛው መንገድ... ማባዛት በጭራሽ አይቻላችሁም። እንዲህ ሲጋጠም፡ በትክክል ገጥሞ በትክክል አንድ መሆን አለበት።

136 አሁን፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ምን እያሳየው ነበር ምን እያደረገ ነበር? የአብርሃምን ዘር በይስሐቅ በኩል፡ ኢየሱስ ዘንድ ይወሰድ ዘንድ እንዳለው፡ እና ወደ ቀራንዮ እንደሚወስደው በዚያም ደግሞ እንደሚከፍለው። መንፈሱን ከስጋው ቀድዶ፡ እንደሚለየው፡ ሥጋውንም አንሥቶ በልዑል እግዚአብሔር ቀኝ እንደሚያቆመው፡ መንፈስ ቅዱስንም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሚልክላት አሳየው። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያ ነው፡ ገነጣጠለው፡ ለእኛ መንፈሱ ደረሰን፡ እርሱ አካሉን ወሰደ። ዳግመኛም ሲመጣ በእኛ ውስጥ የነበረው መንፈስ፡ እንደ ሙሽራ ከእርሱ ጋር አንድ ይሆናል። አሜን። የትኛውም የኃይማኖት ተቋም ወደእርሱ አይጠጋም። አይሆንም፡ ወዳጄ። ባልተበራረዘ፡ በመንፈስ ቅዱስ በመወለድ ብቻ ነው። ይኼው ነው። ቃል ኪዳኑ ይህ ነው።

137 እንግዲህ አሁን፡ "በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ፡" እንዳለው አውቀናል። እና የትኛውም ሰው-ሰራሽ ድርጅቶች ቢነሳ፡ ወይም የኃይማኖት ተቋማት ቢመጡ፡ ኧረ የገሃንም ደጆችም ቢሆኑ አይዘጉትም። ድል ማድረጊያው መንገድ፡ በመቀላቀል ነው። በቃ። በውስጡ መወለድ አለባችሁ እንጂ፡ አትቀላቀሉትም። ትክክል። ስለዚህ ያንን የልዑል አምላክነት መልእክት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅን ማንም ሊያቆመው አይችልም። የገሃነም ደጆች ፈጽሞ አይችሏትም።

138 "ትክክል መሆኑን እንዴት ታውቃለህ፡" ትላላችሁን? በትክክል ከቃሉ ጋር ይስማማል፡ ይህን ማንም ሊቃወመው አይችልም። በትክክል! ቃሉ ነው። መቼም ቢሆን "በአብ፡ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ" ስም፡ የተጠመቀ አንድም ሰው የለም።

139 ታላቁ የኤፌሶን መልአክ፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ ያልተጠመቁትን ሁሉ እንዲህ አዘዛቸው፡ በምንም አይነት መልኩ የተጠመቃችሁ ሁሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያልተጠመቃችሁ ከሆናችሁ፡ መጥታችሁ እንደገና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ እንደሚገባችሁ አደራ ሰጥቷችኋል። "ከዚህ ትምህርት ሌላ የሚያስተምር፡ መልአክ ከሰማይ እንኳ ቢወርድ የተረገመ ይሁን፡" አለ።

140 ስለዚህ በዚህ በመጨረሻው ዘመን የሚመጣው መልአክ ምን እንደሆነ ማየት ትችላላችሁ፡ ሲወጣ ምን አይነት መልእክት ይኖረዋል። ወደ እሱ እየተመራን ይሆናል። እኔ ግን እላችኋለሁ፡ እሱ ሲመጣ፡ ጥምቀትን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሰብካል። ይህን ካላመናችሁ፡ ነገ ማታ ወደዚህ ብቅ በሉና ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አሳያችኋለሁ። እነዚህ በርግጥ ያደርጋል! የልብ መገረዝ፡ መለኮታዊ ተአምራቶች፡ በጴንጤቆስጤ ዘመን እንደነበራቸው የኃይል ስራዎች ሁሉ። ዋናው የጴንጤቆስጤ በረከት እሷን ለመውሰድ ወደዚያ ወደ

ትንሿ ቅሪት ይመለሳል። ያ ውል ልክ መጀመሪያ ሲታረድ እንደነበረበት እንዲሁ ይሆናል። ኦህ፡ እኔስ እወደዋለሁ! ደስ ብሎኛል፡ በጣም ደስ ብሎኛል። በበቂ ሁኔታ ልገልጸው—አልችልም። ከነሱ ጋር አንዱ ማለቴ ደስተኛ ነኝ። ደስ ብሎኛል!

141 ወንድሞቼ ሁሉ እንደዚህ ቢሆኑ ብዬ እመኛለሁ። ወንድሞቼን እና እህቶቼን፡ ውድ ጓደኞቼ ሁሉ ከዓለም ዘንድ አውጥቼ፡ ይህን ታላቅ ነገር ማየት እንዲችሉ እመኛለሁ። እግዚአብሔር ይህን ያውቃል፡ ዛሬም እንኳ ቢሆን፡ ለመሄድ ፈ—ፈ—ፈቃደኛ፡ እሆናለሁ። ገና የማሳድገው፡ ልጄ ዮሴፍ፡ አለ፡ ህጻናት ሴቶች ልጆቼ፡ ሳራ እና ርብቃ፡ እንዲሁም ትቻት ላለመሄድ የምሳሳላት ሚስት አለችኝ፡ ነገር ግን ወንድሞቼ እና-... በዚህች አለም የማውቃቸው ሰዎች፡ ይህ ተቀብለው እንደሚያምኑ እና፡ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መፈለጋቸውን ካወቅኩ፡ አሁኑኑ ለመሄድ ዝግጁ ነኝ። በትክክል እውነት ነው። አያችሁ? እንደው፡ ብችል ኖሮ... ደግሞም... በጨዋነት ስታናግሯቸው፡ የሆነ ነገር ልታደርጓቸው እንደፈለጋችሁ አርገው ያስባሉ። እና—ማድረግ ያለባችሁ አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ይህም በትክክል ከቃሉ ጋር ጸንታችሁ በደንብ ቸንክሩት። እና ያ ትክክል ነው፡ በትክክል ከእሱ ጋር ጽኑ። አቤት፡ እንዴት እንደምወደው!

142 የእርሱ የበላይ የሆነው፡ የአምላክነቱ መገለጥ ነው። ምን፡ እንዲሁ አደረገን? እንዲሁ አንጠልጥዬ፡ ልተወው አልችልም። በኤፌሶን ባለችው ቤተክርስቲያን ገልጦታል። ልክ ነው? የክርስትና ብርሃን ፡ ያንን ብርሃን ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው ያን ጊዜ ነው። ልክ ነው? የመንፈስ ቅዱስ ዘመን የጀመረው **እዚህ** በኤፌሶን ነው።

143 ነቢዩም እንዲህ አለ፡ “ሌሊትና ቀን የማይሆን ቀን እነሆ ይመጣል፡ ሲመሽ ግን እነሆ ብርሃን ተመልሶ ይመጣል።” ተረዳችሁት? አያችሁ። እነሆ፡ ይህ የመከራ ቀን፡ አልፎ መጣ፡ አስጨናቂ (ድርጅቶችና እና ሌሎች በሙሉ) መጥተዋል፡ **በዚህ** በመጨረሻው ዘመን ግን፡ ከዚህ ይሄን ያህል በኋላ ላይ እነሆ የተከፈተ በር ሰጠ። ኢየሱስም “በሩ እኔ ነኝ፡” ብሏል።

144 “እኔ በር ነኝ። እኔ መንገድ፡ እውነት እና ብርሃን ነኝ፡” ሲል፡ ሰምታችሁ ታውቃላችሁን? አያችሁ? “ደጁ ውኃ፡ መንገዱም ጠባብ ነው፡” ሲል ሰምታችኋልን? strait እንዴት እንደሚዘረዘር አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? s-t-r-a-i-t፡ ውኃ ነው። ፊደሉ እንዲህ የሆነ strait “ውኃ፡” ማለት ነው። (S-t-r-a-i-g-h-t፡ እዩት።) strait፡ “መንገዱ ውሃ ነው። ውሃውም ደጁ ነው፡ መንገዱም ጠባብ ነው።” ውሃው ምንድን ነው? በር፡ ደጅ ነው። አያችሁ፡ መክፈቻው ነው። “በጌታ በኢየሱስ ስም፡ መንገዱ በውሃ ውስጥ ነው። ደጁ ውኃ ነው፡ መንገዱም ጠባብ ነው፡ ይህም... ” ኢየሱስ... “በጌታ በኢየሱስ ስም፡ መግቢያው ደጅ፡ ውኃ ነው።”

145 “ንስሐ ግቡ እያንዳንዳችሁ ለኃጢአቶቻችሁ ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ወደ ቀራንዮ ስትመለከቱም፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ፡ ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ነውና።” (አንዳንዶቹ “ለሐዋርያቱ ብቻ ነው፡” ይላሉ።) “ለእናንተና ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችንም ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው።” ይኸው—ይኸው ነው። “ጌታ

አምላካችንም ለሚጠራቸው ሁሉ ነው።” የመድሃኒት ማዘዣው በተጻፈበት መልኩ ካነባብችሁት፡ የተሰፋው ቃል ለሁሉም ነው። በትክክል።

146 “እንግዲህ፡ በዚህ በኩል እሾልካለሁ፡” አትበሉ።

147 እያችሁ፡ አንድ ሰው አንድ ጊዜ ሾልኮ፡ መጨረሻው ሌላ ነገር ሆነ። ይህን ታውቃላችሁ? ምሳሌውን እንብባችሁት ታውቃላችሁ? ሾልኮ የገባውን ሰው ሌላ ነገር ውስጥ ደረሰ። እንግዲህ፡ ከወደ ምሰራቃውያን፡ ወደ—ወደ ሰርግ እራት ሲሄዱ... ጠዋት ላይ እናነሳዋለን፡ ያ ሰው፡ እንዴት ወደ ሠርግ እራት ላይ እንደገባ። ጠዋት ለማየት፡ እንሞክራለን። አሁን ልናገር አሰቤ ነበር፡ ግን እተዋወዋለሁ። ለጠዋት ይሁን፤ ያ ሰው ከሠርግ እራት... ወይም፡ ወደ ሠርግ እራት ወደዚያ ቦታ እንዴት እንደገባ።

148 መልካም እንግዲህ፡ “ደጁ ውኃ ነው፡ መንገዱም ጠባብ ነው።” ወደ ጌታ እግዚአብሔር መግቢያው ደጅ፡ ውኃ ነው።

149 “የተከፈተውን በር ሰጥቼሃለሁ። መክፈቻዎቹን ይዣለሁ። መክፈት የምችለው እኔ ብቻ ነኝ፡ የምገልጠው እኔ ብቻ ነኝ፡ መክፈቻዎች አሉኝ።” ልክ ነው? “አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፡ አብም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።” ማንም ሰው ሊድን የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንጂ፡ በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን፡ በማንኛውም ድርጅት፡ በማንኛውም ቢሾፕ፡ ጳጳስ አይደለም። እሱ መክፈቻዎቹን ይዟል፡ አቅም ያለው እርሱ ብቻ ነው... የምን መክፈቻዎች? ዳዊት፡ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥበት የመጪው ሚሊኒየም። “የዳዊት መክፈቻዎች አሉኝ፡ እኔም በሩን እከፍታለሁ ማንም ሊዘጋው አይችልም። ከእኔ በቀር ማንም ሊከፍተው አይችልም፡ እና ማንም ሊዘጋብኝ አይችልም።”

150 እንዴት ሊሆን ይችላል? ራሱን እስኪገለጥለት ድረስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ሰው እንዴት ሊያውቅ ይችላል? እያችሁ፡ ራሱን ይገልጣል፡ መክፈቻም ይዟል። ሊከፍተውም ሊተወውም ይችላል። እያችሁ? “የበር መክፈቻ አለኝ። በሩ እኔ ነኝ። እኔ መንገድ ነኝ። እኔ ህይወት ነኝ። እኔ ብርሃን ነኝ።” ኦህ! “እኔ አልፋ ነኝ። እኔ ኦሜጋ ነኝ። እኔ ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ። እኔ አብ ነኝ። እኔ ወልድ ነኝ። እኔ መንፈስ ቅዱስ ነኝ። **እኔ ነኝ!** እንጂ ‘ነበርኩ’ ወይም ‘እሆናለሁ’ አይደለም። **እኔ ያ ነኝ እኔ ነኝ**፡ ያም—ነገሩን ሁሉ ያስረዳል። **እኔ ነኝ!** ‘ነበርኩ’ ወይም ‘እሆናለሁ’ አይደለም። **እኔ ነኝ**፡ ይህ ማለት ‘ለዘለአለም በህያውነት የሚኖር’ ማለት ነው። እያችሁ፡ **እኔ ነኝ!** ሁሌም የነበረ፡ ሁሌም የሚኖር፡ ሁሌም እንደነበርኩ ሁሌም እንደምኖር አሁንም እኔ ነኝ፡” እያችሁ፡ እሱ—**እኔ ነኝ** ነው!

151 የዳዊት መንግሥት መክፈቻዎች አለው፡ “ማንም አይዘጋውም።” 7ኛው ቁጥር፡ የዳዊት መክፈቻ እንዳለው፡ በትክክል ያረጋግጣል፡ “ማንም አይዘጋውም!”

152 አሁን የሚቀጥለው ነገር ምን እንደሆነ፡ በፍጥነት እንይ፦

### ... ኃይልህ ታናሽ ቢሆንም፡...

153 ኦህ! እዚህ ጋል ላለው ታናሽ መንጋ “ኃይልህ ታናሽ ነው፡” ይለዋል። ያ ማለት ምን ማለት ነው? ሙት የነበረ ሰው፡ ሕያው ሆኖ፡ ህይወት ዘርቶ፡ ትንሽ ሲነቃ፡ ራሱን እንደሚነቀንቅ ነገር ነው። ካረጁ እና ከሞቱ የሃይማኖት

መግለጫዎች እና ከነገሮች ሁሉ ተላቀህ፡ ትንሽ ወደ ሕይወት መምጣት ጀምረሃል፡ ራስህን ነቅንቀሃል፡ እራስህን ማነቃቃት ጀምረሃል ነው። “ትንሽ ኃይል አግኝተሃል፡ እኔ ግን በፊትህ በር ሰጥቼሃለሁ።” ልክ ከሉተራኒዝም እና ከፓፓሊዝም—እና ከሌሎች፡ ኢዝሞች ሁሉ፡ እና—እና ከሜቶዲስትዝም እና ከልዩ ልዩ ነገሮች እንደወጡ፡ እንዲህ አለ፦ “ከፊትህ በር ሰጥቼሃለሁ፡ አሁን ትንሽ ኃይል አግኝተሃል፡ እስኪ እንዴት እንዴት ታደርገዋለሁ? በፊትህ ተዘጋጅቶልሃል፡ አንተ እንደፈለግክ፡ መግባትም ምወጣትም ትችላለህ። በሩ በፊትህ ተዘጋቷል። ትንሽ ኃይል አግኝተሃል፡ ወደ ህይወት እናስራራህ ነው፡ ጅማሬ ላይ ነህ።”

154 የቀደመችው ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ነበር። በሎዶቅያ ዘመን መገባደጃ ላይ፡ እንደገና ወደ ሥራ ተመለሰች። አሁን እዚህ ላይ ልብ ካላችሁ፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ በሁለቱ መካከል እንዳለች ለ—ለማሳየት ነው። ወደ ሎዶቅያ ዘመን፡ ወይም ወደ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ስትገቡ፡ “ሥራህን አውቃለሁ፡” ልክ በሎዶቅያ ዘመን መጨረሻ ላይ። ምን ነበር? “ሥራህህን፡ ሰይጣን ያለበት መቀመጫ ነው።” የሰይጣን መቀመጫ ምን ነበር? አያችሁ፡ እንደገና በቀጥታ ወደ ኃይማኖት ተቋማት ተመለሰች።

155 እናንተ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ፡ እና የጴንጤቆስጣል ዋንነስ፡ እና ቸርች ኦፍ ጋድ ሆይ! ወንድሞቼ፡ ያደረጋችሁትን ነገር፡ አይታያችሁምን? በቀጥታ እግዚአብሔር ወደሚጠላው ነገር ተመልሳቿል፡ ወንድማማችነትን አፍርሳቿል። አሴምብሊስ ኦፍ ጋድን ተመልከቷቸው፡ በዓለም ላይ ካሉት ምርጥ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ናቸው። የተባበሩት የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያንን ተመልከቷቸው፡ በህይወታችሁ አይታችሁ የማታውቁት ድንቅ ናቸው። ቸርች ኦፍ ጋድን ተመልከቷቸው። በእነዚያ ድርጅቶች ምክንያት ብቻ፡ እርስ በርስ ይሳሳባሉ ይመካካሉ ይነጫነጫሉ፡ እርስ በርሳችሁም “ጥንብ አንሳ” እና “የዋሻ አይጥ” ይባባላሉ። ለምን፡ ውርደት ነው!

156 እግዚአብሔር የሚጠላው አንድ ነገር “በወንድማማቾች መካከል ጠብን መዝራት ነው።” እና ትክክል ነው። በወንድማማቾች መካከል ጠብን የሚዘሩ፡ እነዚያ ድርጅቶች ናቸው። በመሃል ቆመን “ወንድማማቾች ነን!” ማለት አለብን፡

> አንከፋፈልም፡
> አንድ አካል ነን፡
> አንዱ በተስፋ እና በትምህርት፡ (በመጽሐፍ ቅዱስ
> ትምህርት።)
> አንዱ በፍቅር።

157 **ክርስቲያን ወታደሮች ሆይ፡ ወደፊት**፡ የሚለውን የድሮ መዝሙር እወደዋለሁ። አዎን፡ ወዳጄ።

158 የሎዶቅያ የመጨረሻ ሰዎች፡ እንደገና ወደ ሥራ ተመለሱ፡ ወይም የጴንጤቆስጤ ተቋሞች ወደ ኃይማኖት ተቋም ተመለሱ። ቁጥር 15 ን እንይ፡ እዚህ ደርሻለሁ፡ “ራዕይ 3 ቁጥር 15።” ትክክል ካልሆነ፡ አሁን እዩት። ራዕይ 3፡ እ—እና፡ ወይም፡ ያንን በትክክል እንደጻፍኩት እንይ። ራዕይ... ኦህ፡

አይደለም፡ አይደለም፡ እኔ—ተሳስቻለሁ፡ ቁጥር 15 ነው። የዚህ ተመሳሳይ ምዕራፍ ቁጥር 15 ነው፡ እዚህ ላይ ተመሳሳይ ነገር ያሳያል። አዎን፡ ኸሃ-ሃህ፡

### በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ፡ ሥራህን አውቃለሁ፡...

159 "ሥራህን አውቃለሁ።" እንደገና ወደ መጀመሪያው ነገር እንደተመለሱ ያሳያል። እስከነኃይላቸው ተመልሰው ወደ ጴንጤቆስጤ ተቋም ገቡ። እዚሁ ምዕራፍ ላይ—15ኛው ቁጥር። መልካም እንግዲህ።

160 በሁለቱ ዘመናት መካከል፡ በሁለቱ የኒቆላውያን አስተምህሮ ተቋም ዘመናት መካከል ትንሽ ኃይል ይዘዋል። እንግዲህ፡ እዚህ ያሉት ሉተራን ሲመሰርቱ፡ ወደ ኒቆላውያን፡ ወደ ታላላቅ ሊቀ ጳጳሳት እና ወደ መሳሰሉት ተመለሱ። ከዚያም ዌስሊ መጣ፡ የካንተርበሪን ሊቀ ጳጳስ እና እነዚህን ሁሉ በዚያ ዘመን ውስጥ፡ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እና በመሳሰሉት—ታላላቅ ነገሮች መሰረቱ። አሁንም እዚህ ጋር ደግሞ ጴንጤቆስጤዎች፡ እንደገና ወደ ተመሳሳይ ነገር፡ ወደ ታላላቅ የኃይማኖት ተቋሞቻቸው፡ ወደ ኒቆላውያን አስትምህሮ ተመልሰዋል። በእነዚህ ሁለት ዘመናት መካከል ግን በሩን ከፍቶ ለቤተ ክርስቲያን ትንሽ ኃይል ሰጠ ራሱን መነቅነቅ የሚያስችለው በቂ ኃይል ሰጠው፡ ወደኋላችሁ ተመልከታችሁ እዩ፡ የት እንደነበረም መገለጡን አግኙት። ዞር በሉ፡ እና ሁሉንም እዩት (ታውቃላችሁ፡ ተዘርሯል)፡ መጀመሪያ ማወቅ ያለባችሁ ግን፡ ጭንቅላቱን ማንቀሳቀስ ጀመረ እና ዙርያውን ተመልክቶ ጭንቅላቱን አንቀሳቀሰ።

161 በነገራችን ላይ፡ ትናንት ምሽት ስለዚያ ህልም እያየሁ ነበር። ቻርሊ፡ ሽኮኮ በጥይት የመታሁ ይመስለኛል፡ ከቅርንጫፍ ላይ አወረድኩት። እና እዚያ ውስጥ አንዲት አሮጊት ሴት አየሁ። ኦህ፡ ተናዳብኛ ነበረችና፡ ልትይዘኝ፡ ወደ እኔ መጣች። እናም ይህ ሽኮኮ በአንገቱ ላይ ትንሽ ነጭ ክር ነበረው። እናም ያ ምስኪን እዚያ ወድቆ ሁለት ሶስት ጊዜ ራሱን ነቀነቀ እና አየኝ፡ እና የቻለውን ያህል ተነሣና፡ ወደ ጫካው ተመለሰ።

162 ታውቃላችሁ፡ አሮጊቷ ምናልባት ቤተክርስትያን ማለትም ልትሆን ትችላለች። ልትሆን አትችልም ወይ? ልትደበድበኝ ሞከረች፡ በሆነ መንገድ ከሷ ራቅኩ። እና... ኦህ፡ ግን'ኮ፡ ትንሽ ብርሃን ብቻ ነው፡ ለማወቅ ግን በቂ ነው—ወደ... ወደ ጎዳናው እንደወጣሁ ትዝ ይለኛል እሷም በዚያ ልታርደኝ ትፈልጋለች፡ እና ፎርዴን በፍጥነት አዞርኩት፡ በጀርባ ላይ ተጎታች ነበራቸው፡ እና እሷ እንዳትይዘኝ ፈልገው፡ ዕቃዎቹን ሁሉ ሸፈኑኝ፡ እና በሌላ መንገድ ሄድኩ። በዚህም ተረፍኩ።

163 "አሁን፡ ትንሽ ኃይል ቀርቶሃል፡ ስለዚህ ይህን ኃይል በሁለቱ የኃይማኖት ተቋማት መካከል ፊት-ለፊት ለመመለስ ለመጠቀም ትፈልጋለህ።" አስተዋላችሁ? "ቃሌን ጠብቀሃል!" የሚቀጥለውን ጥቅስ አሁን ተመልከቱ፡-

### ... ኃይልህ ትንሽ ቢሆን፡ ቃሌን ጠብቀሃልና፡...

164 "ቃሌን ጠብቀሃል፡" ኃይል ያገኙት በዚህ መንገድ ነው። መገለጡን ያገኙት በዚህ መንገድ ነው። ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን ሲያትም መጽሐፍ ቅዱስን ያገኙት ሁሉ፡ ከዚያ በመቀጠል እስከ ዌስሊ እና በሌሎች ዘመንም ድረስ መጥታል፡ እነሱም ቃሉን ጠብቀው ይዘውታል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሥጋ የሆነው እግዚአብሔር በመካከላችን ሲገለጥ፡ እና የውሃ ጥምቀት በኢየሱስ

ስም እንደሆነ አይተው፡ ተንደርድረው ወደ እሷ ገቡ። ይኸው ነው። ያኔም—ያኔ ሰሙን ነበራቸው። አያችሁ? እንዴ፡ ግልጽ'ኮ ነው… ጋዜጣ ከማንበብ የበለጠ ግልፅ ነው። አያችሁ? እንደው… መካድ አይቻልም፡ ምክንያቱ እዚህ ጋር ነው። እዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተስሏል፡ እናም እዚህ እዚህ አለ፡ ደርሰንበታል… ታሪክ ነው። የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ሰያሜ ያገኘችበት በ1908፡ 10፡ 12፡ አካባቢ ይጀምራል፡ መውደቅ የጀመረችው፡ በዚያ ጊዜ አካባቢ ነው።

165 እንግዲ መልካም፡ አሁን፦

**… እና ሰሙን አልካድክም… ሰሜን አልካድክም።**

166 አሁን፡ ደስ ይላል። የዳዊትን—መክፈቻዎች አሉት፡ ቃሉን መጠበቅ ይችላል—ወደ መንግሥቱም ያስገባችኋል። ሰሙ ተገለጠ። "ስም እያላት ከሞተችው" ቤተ ክርስትያን ወጥተው፡ አሁን ህይወት ያለው ሰም ወዳላት፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ገብተዋል። አያችሁ? ኑ ከሙታንም መካከል ተለዩ፡ "አብ፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ።" "አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ" ብሎ ሰም፡ ምንም ትርጉም እንኳን አይሰጥም። አያችሁ፡ ለመገለጥ የተተወ ነው። መጽሐፉ በሙሉ የተፃፈው በመገለጥ ላይ ነው። ነገሩ ሁሉ ይህ ነው፡ እራሱን ይገልጣል።

167 አሁን እንግዲህ ማቴዎስ 28፡19 ላይ፡ "ሂዱ ህዝቡን ሁሉ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም አጥምቁ፡" አላቸው። አሁን፡ ከነዚህ ውስጥ የትኛውን ሰሞች ልትጠቀሙ ነው? አሁን፡ አብዛኛው የሥላሴ እምነት ተከታዮች የሚጠመቁት፡ "በአብ ሰም፡ በወልድ ሰም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም ነው።" መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንኳን አይደለም። ማንንም ጠይቁ። አለመሆኑም ተረዱ… በነጠላ፡ **ሰም** እንጂ፡ **በሰሞች** አይልም። **ሰም!** የአብ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ሰም። አያችሁ? መልካም። አባት ሰም አይደለም፡ ልጅ ሰም አይደለም፡ መንፈስ ቅዱስ ሰም አይደለም። ታዲያ ምንድን ነው? የሞተ ነገር! ምንም ሰም የለበትም። ነገር ግን በእነዚያ በሞቱ መጠሪያዎች…

168 በክርሰቶስ ሕይወት፡ የሚገለጥ ነው። ጴጥሮስም የመንግሥተ ሰማያት… መክፈቻዎቹን በእጁ ይዞ—በዚያ ሰፍራ ቆሞ ነበር፡ መንግሥቱም መንፈስ ቅዱስ ነው፡ የመንግሥቱ መክፈቻዎች፡ ጎኑ ላይ ተንጠልጥለው ነበር። በሌላ አነጋገር፡ መገለጥ ነው፡ ኢየሱስ ነግሮት ነበርና። ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ አይታይህም ወይ? የእውነትን መገለጥ የተቸረው ለጴጥሮስ ነበረ። ኢየሱስ በተናገራቸው ጊዜ፡ በዚያ አጠገብ ቆሞ ነበርና፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም እያጠመቃችኋቸው።"

169 ብሎ በተናገራቸው ጊዜ ጴጥሮስ ዞር ብሎ፡ "ጌታ ሆይ፡ መክፈቻዎቹን እዚህ ጋር አገኘኋቸው። ያ ምን ማለት እንደሆነ መገለጡ ተረድቼዋለሁ፡ ምክንያቱ አብን ሰም አይደለምና፡ ወልድ ሰም አይደልም፡ መንፈስ ቅዱሰም ሰም አይደለም፡ ያ ሰም ማን እንደሆነ ግን አሁን አውቄዋለሁ።" "ስለዚህ በጌታ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም አጠምቃችኋለሁ።" አሜን። ዋው! ትክክል ነው።

170 አሁን፡ ልክ የፍቅር ታሪክ እንደማንበብ ነው። እናንተም… እንግዲህ ያ የማቴዎስ መጽሐፍ፡ የመጨረሻው ክፍል ነው። ለምሳሌ አንዳንዶቻችሁ ሴቶች፡ የፍቅር ታሪክ አንሰታችሁ… እንደማታደርጉት አውቃለሁ፡ እንደማታነሱ እርግጠኛ ነኝ፡ አይ፡ አይ። አያችሁ? ነገር ግን ሐጢአተኞች ሳላችሁ እንደዚያ ብታደርጉ፡

አያችሁ፡ ታሪኩን ከሆነ ነገር ላይ አንስታችሁ... ታውቃላችሁ፡ እናንተ ገና ወጣት ሴቶች ሳላችሁ፡ ይህ ታሪክ አንብባችሁ ይሆናል፡ እንዲህ የሚል፡ “ጆን እና ሜሪ በደስታ ኖሩ።” ኸሃ! ጆን እና ሜሪ ማን ናቸው? አሁን፡ ጆን እና ሜሪ ማን እንደሆኑ የምታውቁበት ብቸኛው መንገድ ይህ ብቻ ነው፡ ይህም፡ ወደ መጽሐፉ አጀማመር ገብታችሁ ማንበብ ነው። አይደል?

171 እንግዲህ፡ በመጨረሻው የማቴዎስ መጽሐፍ፡ በመጨረሻው ጥቅስ ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡ “እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፡ ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው።” እንግዲህ፡ አባት ስም—ካልሆነ፡ ልጅ ስም ካልሆነ፡ እና መንፈስ ቅዱስም ስም ካልሆነ፡ ወደ መጽሐፉ አጀማመር ልትመለሱ ይገባችኋል። አያችሁ? አሁን፡ ወደ መጽሐፉ መጀመሪያ ከገባን፡ ማቴዎስ ምዕራፍ 1፡ ይህ ታገኛላችሁ።

172 ይህች ትንሽ ምሳሌ እዚህ መስጠት እፈልጋለሁ ምክንያቱ በዚህ መንገድ በጭራሽ አይቶት የማያውቅ ሰው ሊኖር ይችላል። ይህን ተመልከቱ፡ **ይህ** አብ ነው፡ **ይህ** ወልድም ነው፡ **ይህም** መንፈስ ቅዱስ ነው። አሁን፡ ተከታተሉ፡ ኢየሱስ በማቴዎስ 28፡19 የተናገረው፡ አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። ልክ ነው? አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ። አሁን፡ **ይህ** ማነው? አባት? ተማሪዎች አዳምጡ። አብ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ወልድ። አሁን፡ **ይህ** ማነው? መንፈስ ቅዱስ ነው። **ይህስ** ማን ነው? [ጉባኤው ሁሉ “አባት ነው፡” አለ።—አርታዒ።] **ይህ** ማን ነው? [ጉባኤው ሁሉ “ልጅ ነው፡” አለ።] ልጅ። መልካም። አሁን፡ ይህ የማን አባት ነበረ? የኢየሱስ ክርስቶስ። ልክ ነው?

173 አሁን፡ የማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 1 ላይ፡ ከቁጥር 28፡ እናንብበው። አሁን የፍቅር ታሪኩን ከፍተን ስለ ምን እንደሚናገር እናየዋለን። ማን እንደሆነ—ይህ ሰው ማን፡ በማን፡ እንዳለ እናየዋለን፡ “ሄዳችሁ በአብ እና፡ በወልድ እና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው።” መልካም። እንግዲህ፡ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 በትውልድ ሐረግ ይጀምራል፡

> **የዳዊት ልጅ፡ የአብርሃም ልጅ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ** ትውልድ **መጽሐፍ።**
>
> **አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፡... ይስሐቅ ያዕቆብን** ወለደ፡...

174 እና እስከ 18ኛው ቁጥር ድረስ—እያለ፡ እያለ፡ እንዲህ እያለ፡ ይወርዳል። አሁን፡ አስተውሉና፡ ወደዚህ ወደ 17ኛው ቁጥር ወደፊት እለፉ...

> **ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት ትውልድ** ነበረ፡ **ከዳዊትም** እስከ **ባቢሎን ምርኮ ድረስ... አሥራ አራት ትውልዶች፡ እና...** ከ**ባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ድረስ አሥራ አራት ትውልድ** ነበረ።
>
> **እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዚህ መንገድ ነበር፡ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በ... ታጨች ጊዜ፡...**

175 ከኋላዬ እያነበባችሁ ነው? በደንብ ተከታተሉኝ፡

> **... እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በ... ታጨች ጊዜ፡... ሳይገናኙ... ልጅ ጸንሳ ተገኘች፡** የእግዚአብሔር **ልጅ ጸንሣ ተገኘች** የአብ።

176 የሚነበበው እንደዚያ ነውን? ከማን ልጅ ጋር ተገኘች? [ጉባኤውም "**የመንፈስ ቅዱስ፡**" አለ።—አርታዒ።] እንግዲህ፡ አንድ ሰው አባቱ **ይህ** ነው ያለ መሰለኝ። እንግዲህ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ ሰው ከሆነ፡ አብ ሌላ ሰው ከሆነ፡ እንግዲያውስ ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነው። የሚወለድውስ ምን ይሆናል? ህጋዊ ያልሆነ ልጅ። "ኦህ፡" እናንተም ትላላችሁ፡ "እ... ዝም ብላችሁ ነካ አርጋችሁ ታልፋላችሁ።" መልካም፡

**ባልዋም ዮሴፍ፡ ጻድቅ ሰው ሰለ ነበረ... እ... በሰዎች ፊት መቀጣጫ ሊያደርጋት ሰላልፈለገ፡ በሰውር ሊተዋት አሰበ።**

**እርሱ ግን ይህን ሲያሰብ፡ እነሆ፡ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፡ እንዲህም አለው፡ የዳዊት ልጅ፡ ዮሴፍ ሆይ፡ ሚሰትህን ማርያምን ወደ አንተ ለመውሰድ አትፍራ፡ በእርሷ ውስጥ የተፀነሰው የማን ነውና...** [ጉባኤው ሁሉ "**ከመንፈስ ቅዱስ**፡" አለ።]

177 "በሁለት ወይም በሦስት አፍ ምሰክሮች፡ ቃል ሁሉ ይጸናል።" አያችሁ? ኧሃ-ሃህ። መንፈስ ቅዱስ አባቱ ነበር። እንግዲህ፡ ራሱ ደግሞ "እግዚአብሔር" አባቴ ነው ብሏል። ስለዚህ፡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ከሆኑ፡ የትኛው አባቱ ነበር? እራሳችሁን ምን ውስጥ እንደምትከቱ ተመልከቱ። እራሳችሁን በአየር መካከል ማንጠልጠል ብቻ ይሆንባችኋል። አያችሁ? እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱ ነው ማለት አለባችሁ! መንፈስ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር ነው። (እንግዲህ፡ ከሶስት ይልቅ፡ ሁለት ናቸው ማለት ነዋ።) መልካም።

178 መልካም፡ 21ኛው ቁጥር ላይ፡

... **በእሷ ውስጥ የተፀነሰው...** (ማን አሰቀመጠው... በእሷ ውስጥ ያፀነሰው ማን ነበር? መንፈስ ቅዱስ። መልካም።)

**ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና፡ ሰሙን** (ሰሙን) **ኢየሱስ ትለዋ**ለህ።

**... ይህ የሆነው ሁሉ፡... አሁን የሆነው ነገር ሁሉ፡ ከጌታ በነቢይ የተነገረው፡ ይፈጸም ዘንድ ነው፡**

**እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች፡ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡ ሰሙንም እማኑኤል ይሉታል፡... ትርጉሙም... እግዚአብሔር ከኛ ጋር ማለት ነው።**

179 ሰሙ ማን ነበር? ሰለዚህ፡ ቀሪ ዘመናቸው በደስታ የኖሩት ጆን እና ሜሪ እነማን ናቸው? የአብ፡ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ሰም ማን ይባላል? ኢየሱስ በምድር ሲወለድ፡ ክርስቶስ ጌታ ነበር። በተገረዘ ለታ (ከሰምንት ቀን በኋላ) እናቱ ሰም አወጣችለት አባቱም ሰም ሰጠው "ኢየሱስ።" ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ፡ ያኔ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተባለ።

180 ጌታ ነበረ! ሲወለድ፡ ክርስቶስ ጌታ ነበረ። ከዚያም "ኢየሱስ፡" የተባለበት ሰሙን በተቀበለ ጊዜ ጌታ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን ሆነ። ለጴጥሮስ የተገለጠው ይህ ነው፡ ዮሐንስና ማርያም ማን እንደሆኑ ገብቶታል እንዲህ ባላቸው ጊዜ፦ "ሂዱና በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም አጥመቁ።" ሰለዚህ፡ ኢየሱስ ጴጥሮስ የመገለጥ ሰጦታ እንዳለው ሰለሚያውቅ ሊገለጠው

ይችላል፡ አስቀድሞ ከላይ ከሰማይ በመንፈስ ስለ ተገለጠለት፡ አውቋል። እግዚአብሔርም አንድ ሰው ከላይ መገለጦችን መቀበል እንደሚችል ሲያየው፡ ያንን ሰው ያምነዋል፡ በእርሱም አንድ ነገር ያደርጋል፡ በተገለጠለት ጊዜም፡ እንዲህ ብሎታልና፡ “ከአባቴ በቀር ይህን ማንም ሊገልጥ አይችልም።” ሊገልጠው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡ ጴጥሮስንም ከመንፈሱ ጋር... ንክኪ ማድረጉን አውቆታል። ስለዚህ...

181 ጴጥሮስም መገለጡን አውቆ፡ ወደዚያ ወጣና እንዲህ አለ፡ “ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።”

182 እንግዲህ፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ኢየሱስ ለጴጥሮስን እንዲህ ብሎ ነበር፡ (መገለጡ ማን እንደሆነ በነገረው ጊዜ፡ “በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።”)፡ “እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ መክፈቻዎቹም እሰጥሃለሁ።” ኦህ! “ወደ መንግሥቱ መግቢያ ቁልፎች! መክፈቻዎችን እሰጥሃለሁ። በምድር የምታስረው ሁሉ፡ እኔ በሰማይ አስረዋለሁ። በምድር የምትፈታውን ሁሉ፡ በሰማይ እፈታዋለሁ።”

183 ከዚያም በጰንጠቆስጤ ቀን፡ በቤተክርስቲያን ምርቃት ቀን፡ ኢየሱስ ከተናገረው ከአሥር ቀን በኋላ እንዲህ አላቸው “እንግዲህ ሂዱና—በአብ፡ በወልድ፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ፡” ጴጥሮስ በመንፈሳዊ መገለጥ “አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ” የሚባል ስም እንደሌለ አውቋል። እንግዲህ፡ እስከ ካቶሊክ ዘመን ድረስ ይህን ማንም አላሰበም። በነገራችን ላይ “በአብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ” ስም የተጠመቀ ሰው ሁሉ ጥምቀቱ የተጠመቀው በካቶሊክ እምነት ነው፡ (በትክክል) የክርስትያን ጥምቀት አይደለም። ቅሪቶች... ነበሩ።

184 እንግዲህ፡ በጰንጠቆስጤ ቀን፡ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡ እና በልሳኖች ተናገሩ—እንደሰከረ ሰው ሆኑ። የሰከሩትም፡ በአዲስ ወይን ሰከሩ። ከላይኛው ቃና ከሰማይ በወረደው፡ በአዲሱ የወይን ጠጅ ሰከሩ። እናም ሁሉም እየጮሁ እና እልል እያሉ እንደ ሰከረ ሰው በሆኑ ጊዜ፡ ጴጥሮስም በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ አላቸው “ሰክረው አይደለም፡ ነገር ግን ይህ—ነገር... በነቢይ ‘መንፈሴን እፈሳለሁ፡’ ያለውን እንደሚፈጸም አስቀድሞ የተነገረ ነው።”

185 እና አሁን እነሱም—አሉ፡ “ወንድሞች ሆይ፡ ምን እናድርግ? ወንድሞች ሆይ፡ ምን እናድርግ? ” ጥያቄው ይህ ነው። “እንዴት እንገኘዋለን? ቁልፎቹን የያዘው ማነው? ”

186 “ስምዖን ሆይ፡ ቅረብ። መክፈቻዎችን ይዘሃል፡ በል ከኅንህ አውጣቸው። እስኪ ምን ትላቸዋለህ? እንግዲህ አሁን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን አስታውሱ፡ ‘በምድር ያሰርከው፡ እኔ በሰማይ አስረዋለሁ። በምድር የፈታኸው፡ እኔ በሰማይ እፈታዋለሁ።’ እንግዲህ አምላክ ከሆነ፡ ቃሉን ይጠብቃል።”

187 አሁ፡ እናንተ የካቶሊክ ካህናት ሆይ፡ እስኪ “የኃጢአት ስርየታችሁን” አሳዩን። አንድ የካቶሊክ ቄስ አንድ ጊዜ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ኢየሱስ፡ ‘ሐጢአታቸውን የምትተውላቸው፡ ይተውላችኋል’ አላለምን? ”

እኔም “ብሏል፡” አልኩት።

"'ሐጢአታቸውን የያዛችሁባቸው፡ ይያዝባቸዋል'? "

"አዎን።"

"ያ ማለት ይቅር ያላችኋቸው፡ ይቅር ይባላሉ፡ ይቅር ያላላችኋቸው፡ ይቅር አይባሉም ማለት ነው።"

"የተናገረው በትክክል ይህ ነው፡" አልኩት።

እንዲህ አለ፡ "ታዲያ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ፡ ቤተ ክርስቲያኑም እኛ ነንና፡ በምድር ላይ ኃጢአትን የማስተሰረይ ስልጣን አልሰጠንምን? "

188 "በእርግጥ ሰጥቶናል።" "አሁን፡ እነርሱ ይቅር እንዳሏቸው እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይቅር ብትሏቸው፡ እኔም ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡" አልኩት። አዎን። አልኩትም፡ "በምን መልኩ ነበር እነሱ ይቅር ያሏቸው? እናንተ እንደምታደርጉት፡ 'ዳዊትን ድገሙ' ወይም ሌላ ነገር አድርጉ፡ ትሏቸዋላችሁን? "

189 አይደለም፡ ወዳጄ። ጴጥሮስ ያለው፡ "ንስሓ ግቡ!" አሜን። መክፈቻ ማለት ይህ ነው፡ "ንስሐ ግቡ፡ ለኃጢአቶቻችሁም ስርየት፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታም ትቀበላላችሁ።" ቁልፉ ምድር ላይ "ክሊክ" ባደረገ ጊዜ፡ እነሆ በሰማይ ላይ ደግሞ "ክሊክ" አድረገ። ያ ነው።

190 ስለዚህም ጳውሎስ ኢየሱስን ባጠመቀ ሰው አስቀድመው የተጠመቁትን ጥቂቶችን ባገኘ ጊዜ፡ "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀባላችሁን፡" ብሎ ጠየቃቸው?

እነርሱም፡ አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሰንኳ አልሰማንም አሉት።

እንዲህም አለ፡ "**በምን**… " የግሪክኛ ቃላችሁን መርምሩት፡ እሱ ያለው፡ "ታዲያ **እንዴት** ተጠመቃችሁ? "

እነርሱም "በዮሓንስ፡" አሉት።

እርሱም፡ "ያማ ከእንግዲህ አይሰራም። ሰማይ ዘግቷል። እንደገና መጥታችሁ፡ በ 'ኢየሱስ ክርስቶስ' ስም መጠመቅ አለባችሁ።"

191 ይህንንም በሰሙ ጊዜ፡ ዳግመኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። በተጠመቁ ጊዜም፡ ጳውሎስ እጁን ጫነባቸው፡ መንፈስ ቅዱስም ወረደባቸው፡ በልሳኖችም ተናገሩ ትንቢትም ተናገሩ።

192 ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ወደ መጀመሪያው መመለስ ማለት ይህ ነው። ይህ ልክ ነው። በዚያ የተሰጣቸው "የተከፈተ በር" ማለይ ይህ ነው። በጂኦግራፊካዊ አቀማመጥ ያ ልክ ነው፡ የምሽቱ ብርሃን፡ እና መጻሕፍት በሙሉ በቀጥታ ወደዚህ የሚያመሩ ናቸው።

193 እዚህ ለሰዓታት መቆም እንችላለን፡ እና አስራ አምስት ደቂቃ ብቻ ቀርቶኛል፡ እና ወደ ሰላሣ-አምስት የተለያዩ ነጥቦችን ማስቀመጥ አለብኝ። ካልቻልኩም፡ ምናልባት ዛሬ ማታ ካልጨረሰናቸው ነገ ጠዋት እንዳስሳቸዋለን። መልካም።

194 እንግዲህ፡ መልካም፡

**… ማንምም** ሊዘጋው **አይችልም፡ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን፡ ቃሌን ጠብቀሃልና፡** (መልካም።) **ስሜንም አልካድህምና።**

195 ይኸው ነው! “ስሜንም አልካድህም።” ስም ተገለጠ፡ ከሞተችው የሰርዴስ የኃይማኖት ተቋም ወጥቶ፡ ወደ ህያው ቤተክርስቲያን መጥቷል።

196 አሁን 9ኛውን ቁጥር እናንብበው። አሁን፡ አሁን በደንብ እንከታተላለን፡ በጣም አደገኛ ወደሆነ ነገር እየገባን ነው፦

**እነሆ፡ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን ከሚሉ፡ ነገር ግን ከሚዋሹ፡ ከሰይጣን ማኅበር፡ እንዳንዶችን እሰጥሃለሁ፡ እነሆ፡ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ፡ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ።**

197 እዚህ ጋር፡ ድንቅ መሰናበቻ አለላችሁ። ተመልከቱት! አሁን ምንድን ናቸው? እነዚያ ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ የተናገራቸው፡ ሰሙንም **እዚህ** ጋር ያገኙት፡ “በተከፈተው በር” ገብተው ኢየሱስ ክርስቶስን (የሕይወት ቃል ያገኙ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ፡) አሁንም “ከእናንተ መካከል በሰይጣን ማኅበር ውስጥ ያሉ አሉ፡” ይላቸዋል።

198 አሁን፡ ወንድሜ ሆይ፡ ለአንድ ደቂቃ፡ ወደ ራእይ 2:13፡ ወደ—ጴርጋሞን ከተመለሳችሁ፡ ያ ነገር ማለት የኃይማኖት ተቋም፡ ምን ማለት እንደሆነ አሳያችኋለሁ።

**ሥራህን አውቃለሁ፡ አንተም የምትኖርበት የሰይጣን ዙፋን ባለበት፡ የምትኖርበትን አውቃለሁ፡...**

199 ይኸውላችሁ። ሎዶቅያውያን... ወይም፡ የሐይማኖት ተቋም የሆኑት ኒቆላውያን ቤተክርስትያን ለማለት ፈልጌ ነው። ተመልከት፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ምኩራብ እንደነበሩ፡ ቤተ ክርስትያን እንደነበሩ፡ የሐይማኖት ተቋም ቤተ ክርስቲያን መሆናቸውን ለማሳየት ነው። ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ! “የሰይጣን ማኅበር ናቸው።” ስለዚህ፡ የሐይማኖት ተቋም ሥራዎች የዲያብሎስ ናቸው! እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ ክርስትያኖች አይደሉም፡ ክርስትያን ቢሆኑም፡ የራሱ የሐይማኖት ድርጅት ናቸው። መልካም።

200 አሁንስ፡ እንዲህ እንዳላቸው አስተውላችኋል፡ “በአንተም ዘንድ ‘አይሁድ’ ነን የሚሉ አሉ፡ አንተ ግን ሐሰተኞች ሆነው አግኝተሃቸዋል።”

201 እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ ለታላቁ መልአኩ... የሚናገረው ለማን ነው? በሁለቱ ኣብያተ ክርስቲያናት መካከል ላለችው፡ ለዚህች የተከፈተ በር ቤተ ክርስቲያን።

202 እሺ፡ የመጀመርያዋ የቤተክርስቲያን ዘመን የተማረችው በማን ነበረ? በጳውሎስ። አሁን ወደ ሮሜ ሰዎች 2፡29 እንሂድና አይሁዳዊ ምን እንደ ሆነ እንይ፡ እናንተም ይህን አውቃችሁ—የራሴ ሐሳብ አለመሆኑን ታረጋግጣላችሁ። ወደ ሮሜ ሰዎች፡ ሮሜ ምዕራፍ 2 ላይ፡ ከ 29ኛው ቁጥር። መልካም፡ እንመልከተው፡

**ዳሩ ግን በሰውር አይሁዳዊ የሆነ፡ አይሁዳዊ ነው፡ መገረዝም... በመንፈስ የሚደረግ፡ የልብ መገረዝ፡ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፡ የእርሱ ምስጋና—ከእግዚአብሔር... ነው እንጂ፡ ከሰው አይደለም።**

203 እስኪ አይሁዳዊ—ምንድነው? መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ-ክርስትያን ነው! “‘መንፈስ ቅዱስ ተቀብለናል’ ከሚሉበት ከመቀደስ ዘመን

በኋላ የምትኖርበትን እኔ አውቀዋለሁ፡ እርሱ ግን፡ በጭራሽ አላቸው።" የሚከተሉ ምልክቶች ሳይኖራቸው መንፈስ ቅዱስ ተቀብለናል ይላሉና፡ እርሱ ግን "ውሸታሞች ናቸው፡" አላቸው። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች **ይከተሉአቸዋል።**" ውሸት አታደርጉትምና። ኦህ፡ ወንድም ሆይ! ዙርያ፡ ዙርያህን ሁሉ ይህ አሳውሮባችኋል። አያችሁ? ኦህ፡ ማይ!

> እንሁህም... **እነሆ፡ አይሁዶች ነን የሚሉትን፡ የሰይጣን ማሕበር አደርጋቸዋለሁ፡** ("እነዚያ፡ 'በመንፈስ የተሞላን-ክርስትያኖች' ነን የሚሉትን፡ ሞኩራብ፡ ድርጅት የሆኑትን። የተደራጁትን—ድርጅት ያደረጉትን፡ 'መንፈስ ቅዱስ ተቀብለናል' ብለው እንዲናገሩ አደርጋቸዋለሁ። ገና መገለጡን እንኳን አላገኙትም!" አያችሁ? መልካም።)... እንዲህ እላለሁ... **እንደዚያ ሳይሆኑ፡ አይሁድ ነን** (ክርስቲያኖች ነን የሚሉትን)፡ **ነገር ግን ከሚዋሹ፡ እነሆ፡ መጥተው... በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ፡ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ።**

204 እዚህ የጠዋቱ መልእክት ውስጥ በእኔ ላይ ስንጥቆ መግባት አለበት። እዚህ የምታዩአቸው እነዚህ ሰነፎች ደናግል ናቸው። አያችሁት? ያ መቼ ነበረ? በዘመን ፍጻሜ። ኦህ፡ እነሱ ሲወጡ ጊዜ። ይህ ማለት... አያችሁ? በእምነት ጸድቀው፡ ተቀድሰዋል። በሉተር መልእክት ጸደቁ፡ **እዚህ** ላይ ተቀደሱ፡ "ወደ ተከፈተው በር" ግን አልደረሱም። አያችሁት? በእምነት፡ በሉተር ጽድቅ ነበር፡ ቅድሰናም፡ በዌስሊ ዘመን ነበር።

205 ብዙዎቹ የተወደዱ ናዝሪኖች፡ ፒልግሪም ሆሊነስ፡ ዌስሊያን ሜቶዲስት፡ እና የመሳሰሉት፡ በሙሉ ጥሩ፡ ንጹሕ፡ የተቀደሰ ህይወት ያላቸው፡ መንፈስ ቅዱስን አለን ብለው የሚያስቡ፡ አንድ ሰው በልሳኖች ሲናገር ሲሰሙ፡ ወይም የሆነ ነገር ግን፡ ያፌዙበታል፡ ይቀልዱበታል፡ "የዲያብሎስ ነው፡" ይሉታል። ወንድም ሆይ፡ ይህን ባደርግ ቀን ጥፋትህን በራስህ እጅ ታትማለህ። መንፈስ ቅዱስን ትሳደባለህ፡ ይህም ይቅርታ የለውም።

206 እሺ፡ "እኛ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ነን፡" ትላላችሁ። እኔ የሰንበት አብያተ ክርስቲያናት አባል ብትሆኑም ግድ የለኝም። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡ እና "አይጨምርበትም አይቀንሰበትም።" ትክክል ነው፡ "የሰይጣን ማሕበር!"

207 እንዳልጎዳኋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። እንዲህ—አይነት ንግግር መናገር አልወድም፡ ነገር ግን እንዲህ እንድናገር በውስጤ የሚገፋ ነገር—አያለሁ። ለምን እንደማደርገው አላውቅም። ያንን ማድረግ እንደማልወድ እናንተም ታውቃላችሁ። ስናገር በጣም መጥፎ ስሜት ይሰማኛል፡ መናገር ግን አለብኝ። እንድለው የሚያደርገኝ የሆነ ነገር አለበት። ሴቶችን ስከብድባቸው ሁልጌ እጠላለሁ፡ በጣም—ይሰማኛል... ሴት ልታለቅስ ትችላለች፡ እኔም በጣም አዝናለሁ። ሴቶች ላይ መክበዴ እ—ጠላዋለሁ፡ እንዳደርገው የሚያደርገኝ የሆነ ነገር ግን በውስጡ አለው። አያችሁ? ሰነ ምግባር የጎደላት ሴት (ኦህህ፡ ማን!)፡ እኔ ልቋቋመው አልችልም። ምክንያቱ፡ ከውስጤ እንዳደርገው የሚገፋፋኝ የሆነ ነገር አለ፡ ይህም መንፈስ ቅዱስ ነው።

208 ና እዚህ ከቃሉ ውስጥ ስመለከተው፡ እንዲህ ብዬ እሰባለሁ፡ “ጌታ ሆይ፡ ከተሳሳትኩ፡ አሳየኝ። እንደዚያ ስለመሆን ብቻ እንዳደርገው አትፍቀድልኝ። ሰዎችን... እኔ... እኔ ሰዎችን እወዳለሁ፡ እናንተም ታውቃላችሁና። አምላክ ሆይ፡ እኔ ይህን ማድረግ እንደማልወድ ታውቃለህና፡ ማንም ሰው እንድጎዳ አትፍቀድልኝ።”

209 መንፈስ ቅዱስ ግን ተነስቶ እንዲህ ይላል፡ “በቃሉ ላይ ጸንተህ ቁም! ጽኑ ሁን! በዚያ በቃሉ ላይ ጸንተህ ቁም!”

210 እኔም እላለሁ፡ “እሺ፡ ጌታ ሆይ። እንዲህ ከሆነ... ምርጥ ወዳጄ አንተው ነህ። የምትረዳኝ አንተ ብቻ ነህ... እውነተኛው ጓደኛዬ አንተ ነህ... ይህ ህይወት ሲጠፋ የሚረዳኝ አንድ አንተ ብቻ ነህ፡ ስለዚህ ከአንተ ጋር እቆማለሁ፡ ጌታ ሆይ።”

211 ይኸው መጥቻለሁ። እናንተን ለመጉዳት አይደለምና፡ እነዚያ ድርጅቶች እና ሌሎች ነገሮች ሰቆራርጣቸው እባካችሁ በሌላ አትውሰዱብኝ። ስለዚህ ጉዳይ ምንም ከማወቄ በፊት፡ ከህይወቴ ሁሉ፡ ቆርጬዋለሁና። በፍጹም አምኜው አላውቅም፡ ከዚያ ጋር አብሬ የማልጓዝም ስለዚህ ነው። እና... መልካም ነው። ከዚህ የራቀኝን አምላክ አመሰግናለሁ!

> **እነሆ፡ እንዲሁ ሳይሆኑ፡ አይሁድ ነን** መንፈስ-ተሞልተናል **ከሚሉ፡ ነገር ግን ከሚዋሹ... ከሰይጣን ማኅበር፡ እንዳንዶችን እሰጥሃለሁ፡ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ... አደርጋቸዋለሁ፡...**

212 እንቅልፋምዋ ድንግል በነቃች ጊዜ ትዝ ይላችኋል? እንግዲህ፡ ምን ተብላ እንደተጠራች፡ አስታወሳችሁ? ሙሽራውን ለመገናኘት የወጡ አሰር ነበሩ። ልክ ነው? አምስቱ ልባሞች፡ ዘይት በመብራታቸው ውስጥ ነበራቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘይት ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቅ ሰንት ነው? መንፈስ። ሁሉም፡ እና እያንዳንዳቸው ተቀድሰዋል፡ “አንተ አልተቀደስክም፡ እኔም አልተቀደስኩም... ” ሊል የሚችል፡ አንድም አልነበረም። ሁሉም የተቀደሱ ናቸው፡ አምስቱ ግን (የመገለጥ ጥበብ ለመያዝ) እና ያንን በር ለመያዝ በመንፈስ ለመሞላት፡ አያችሁ፡ እጅግ ልባሞች ነበሩ። በመብራታቸው ውስጥ ዘይት ነበራቸው፡ ሌሎቹ ግን ምንም ዘይት አልነበራቸውም። በተነሱም ጊዜ፡ ለምን፡ እዚህ ወደ እነርሱ መጥተው፡ እንዲህ አሏቸው፡ “ኦህ! ኦህ! ከዘይትሽ፡ ከመንፈስ ቅዱስሽ ጥቂት አካፍይኝ። ጥቂቱን ሰጪኝ!”

213 ያቺም ትላለች፡ “አይ፡ እህቴ ሆይ፡ ይቅርታ፡ ለእኔ የሚበቃ ብቻ ይዣለሁ። የሚተርፍ እንደሌለኝ እርግጠኛ ነኝ።”

214 እና... ከአፍታ በኋላ... እንዲህ አላቸው፡ “ሂዱና ጸልዩ።” እናም ጥቂት ለማግኘት በሄዱ ጊዜ፡ ሙሽራው መጣና ወደ ሰርጉ እራት ገቡ፡ በመከራው ጊዜ ውስጥ ወደሚያልፉበት፡ ወደ ኋላ ቀሩ... ከዚህም በተጨማሪ፡ ሁለት ጥቅሶችን ተመልከቱና፡ ወደ መከራ ጊዜ ውስጥ ሲገቡ ታያላችሁ። አያችሁ?

215 እንግዲህ፡ ሰለ ሰነፎቹ... ነገ ጥዋት እንዳሰሰዋለን። አዎን፡ ትንሽ ብናቆየው የተሻለ እንደሚሆን አምናለሁ፡ ምክንያቱ፡ መዝጊያ ሰአታችን ወደማለቁ እየተጠጋ ነውና፡ መልካም።

216 አሁን እስቲ እንመልከት፦

**እነሆ፡ አደርገዋለሁ...**

ውሸታሞች እንደሆኑ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሌላቸው አወቋቸው።

217 እባካችሁ፡ ሁላችንም አብረን ሳለን፡ ትንሽ ነገር ብቻ ላክልበት። ትናንት ማታ እንዳልኩት፡ የአስቆሮቱ ይሁዳ፡ የጥፋት ልጅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "የጥፋት ልጅ ሆኖ ተወለደ፡" ይለዋልና። ከዚያም እሱ... ኢየሱስ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተወለደ። ከዚያም፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኖረ። ልክ ነው? ሰይጣን... ም በይሁዳ ይኖር ነበር። ያኛው የእግዚአብሔር ልጅ ከነበረ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ከተወለደ፡ ሌላ ዙር የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ከነበረ፡ እንግዲያውስ ሰይጣንም የጥፋት ልጅ ሆኖ የተወለደ፡ በሌላ ዙር የተወለደ... የጥፋት ልጅ፡ ሰይጣን፡ ዲያብሎስ የነበረ ነው።

218 እንግዲህ፡ ካስተዋላችሁ፡ እራሱን **ከ**ኢየሱስ ጋር ተባበረና፡ ከእነሱ እንደ አንዱ ሆነ። አያችሁ? አሁን፡ ያንን ያደረገበት ምክንያት፡ ወደዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን የሚገባ ማታለያ ለማስቀመጥ ነው። እንግዲህ፡ ኢየሱስም "እነዚያ የሰይጣን ማሕበሮች ናቸው፡" ብሏል። ኦህ፡ ማይ! አይገርምም ወይ? የሰይጣን ማሕበር ናቸው! ያ ይሁዳ እራሱን ክርስቲያን ሲያስመስል ነው።

219 የይሁዳ ዋና ነገር ምን ነበር? ገንዘብ ነበር። የዛሬው የብዙዎቹ ከባዱ መጎተቻ ገንዘብ ነው። አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ተመልከቷቸው፡ ማዶ ላይ የሰድሰት-ሚልዮን-ዶላር ህንጻ እየሰሩ ናቸው፡ ትምህርታቸውም "ጌታ አሁን ይመጣል" ነው። "ኦህ፡ እኛን የሚጠራርጉ ቁምቡላዎች ተሰቅለው ተዘጋጅተዋል፡" የሰድሰት-ሚልዮን-ዶላር ህንጻ ይሰራሉ። ኦህ፡ ማይ። እኔ፡ ሃብታም እና የሚያስፈልገኝ... እንደ ጌታ ፈቃድ፡ እንግዲህ፡ ነገ የምናየው ይሆናል።

220 አሁን እዚህ ላይ አስተውሉ። ኦህ፡ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት ትልቅ እንደሆኑ፡ ትልልቅ ድርጅቶች እንደሆኑ ተመልከቱ። ገንዘባቸውን አንድ ላይ ያዋህዳሉ... አቤቱ፡ ማረን! እንደው ባለ መልቲ-ቢሊየን ሆነዋል... የብድር ተቋማት፡ እና የፋይናንስ፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮች አላቸው። አብያተ ክርስትያናት፡ ገንዘብ እና ነዋይ ያበድራሉ። ወንድም ሆይ፡ ያ ለእኔ ሐዋርያዊነት አይመስለኝም።

221 ጴጥሮስም፡ "ብርና ወርቅ የለኝም፡ ያለኝን ግን አለ... " እሱን ሰጡኝና፡ ገንዘቡ ሁሉ ውሰዱ። ትክክል ነው። "ብርና ወርቅ የለኝም፡ ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም... " የነበረው ይህ ነው፡ መገለጡ ነው። "እሰጥሃለሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሰና ተመላለስ።"

222 መልካም፡ አሁን እዚህ እንደምናየው "የሰይጣን ማሕበር ናቸው።" እንግዲህ፡ እንዴት ሊሆኑ ቻሉ? አሁን፡ ይሁዳ በመጣ ጊዜ... አሁን ተከታተሉኝ! ኢየሱስ ወደ ትእይንት በወጣበት ጊዜ፡ ይሁዳ ደግሞ ወደ ትእይንት መጣ። አስተውላችኋል? ልክ ኢየሱስ ከትእይንቱ ሁሉ በወጣበት ቅጽበት፡ ይሁዳም እንዲሁ ከትእይንቱ ጠፋ። ልክ መንፈስ ቅዱስ እንደገና ወደ ትእይንቱ በተመለሰበት ቅጽበት፡ ይሁዳ ወደ ትእይንቱ ተመልሶ መጣ። የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ፡ በማይታዘዙ ልጆች፡ ይሰራ ዘንድ፡ ግድ ያላቸው ስለ መጽሐፍ ቅዱስን ሳይሆን፡ ስለ—ድርጅት ግድ በማለት። አያችሁ? ማሕበር

አደረጓቸው! ኢየሱስም እዚህ ላይ "የሰይጣን ማኅበር ናቸው፡" አለ። የት ናቸው? እስከዚህ ዘመን ድረስ **በዚህ** ተቀምጠዋል። **እዚህ** ላይ እንዴት ተጀመረ? በድርጅት። **እዚህ** ላይ ያደረገው ተመሳሳይ ነገር ነው። "የሰይጣን ማኅበር።" ገባችሁ?

223 "የሰይጣን ማኅበር፡" አለ፡ "በመንፈስ-ተሞልተናል ባዮች።" አሁን፡ እንዴት እንዲህ ሉሉ ይችላሉ?

224 ይሁዳ፡ በምድር ሳለ ከኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ፡ በኢየሱስ አምናለሁ በማለት ተናዟል፡ በዚህም ያለውን ገንዘብ ሁሉ በመያዝ፡ ንብረት ክፍል ሆነ። ልክ ነው? ሁላችሁም ታውቃላችሁ። አሁን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ፡ ጽድቅን (በሐሰት) ተቀበለ። ልክ ነው? በሮሜ 5፡1 ላይ፡ "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን።" ትክክል። መልካም።

225 እንግዲህ፡ ሌላ ነገር፡ በቅዱስ ዮሐንስ 17፡17 ላይ፡ ኢየሱስ እንደተናገረው፡ በእውነት ቀድሳቸው አለ፡ "ቃልህ እውነት ነው፡" እርሱም እውነት ነው።

226 ሄደው የፈውስ ጉባኤዎች እንዲያደርጉ፡ እና አጋንንትን እንዲያወጡ፡ እና ልዩ—ልዩ ተአምራቶችን እንዲያደርጉ፡ በርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣንን ሰጣቸው። ተመልሰው በመጡ ጊዜ፡ ይሁዳም አብሮ ነበር… አሁን ተከታተሉኝ፡ ናዝሪን፡ ዌስሊያን ሜቶዲስት! እጅግ ደስ ብሎአቸው፡ እየተደሰቱ፡ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፡ ተመለሱ፡ አጋንንት ስለ ተገዙላቸውም ጮኹ። ኢየሱስም አላቸው፡ "አጋንንት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ፡ ነገር ግን ስማችሁ በህይወት መጽሐፍ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።"

227 እንግዲህ ይሁዳም ከእነርሱ አንዱ እንደነበር አስታውሱ! እስከዚያው ድረስ ቤተክርስቲያንን ሊያታልል እንደሚችል፡ ተመልከቱት። እሱም በእነዚያ አውታሮች መካከል በትክክል እንደሰራ፡ ታውቃላችሁ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ መገባት ሲጀመር ግን ትክክለኛ ቀለሙ ማሳየት ጀመረ። በእነዚያ-… በሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን፡ እና በሉተራን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደረገውም በትክክል ያው ነው፡ በናዝሪን ቤተ ክርስቲያን፡ እና በቸርች ኦፍ ጋድ እና በሌሎቹ ያደረገው ነገር፡ መቀደስ ድረስ ደርሷል፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እና በልሳኖች ስለ መናገርና፡ ምልክትና ድንቅ ወደ ማድረግ ሲደርስ ግን፡ ኮነኑት።

228 መለኮታዊ ፈውስ ይዘው ሊዞሩአችሁ ይችላሉ። እርግጥ ነው፡ ይሁዳም አድርጓል። አያችሁ? ነገር ግን… ማለት ብዙ መለኮታዊ ፈውስ ይኖራል። ወንድሜ ሆይ፡ ዛሬ ዛሬ በየመንገዱ እየወጡ፡ ለሁለት ሰአታት ቆመው እንዲህ ይላሉ፡ "ለአንድ ምሽት፡ በነጠላ ሃምሳ ዶላር ካልከፈላችሁ ሰብሎቻችሁ ይቃጠላሉ።" እና እንደነዚህ አይነት ነገሮች ሁሉ፡ ዲያቢሎስ ነው። አዎን ነው። በሙሉ ልቤ በመለኮታዊ ፈውስ አምናለሁ። ያ ነግር ግን ከዲያብሎስ ነው፡ ሙሉ በሙሉ፡ ከዲያብሎስ ነው። ምን ያህል ማድረግ እንደምትችሉ፡ እና ምን ያህል እንዳደረጋችሁ ግድ አይለኝም፡ የአስቆርቱ ይሁዳም፡ እንዲሁ አድርጓልና።

229 ኢየሱስም፡ "በዚያ ቀን ብዙዎች ወደ እኔ ይመጣሉ፡ እንዲህም ይሉኛል፡ 'ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ እኔ… በስምህ አጋንንትን አላወጣሁምን ተአምራትስ አላደረግሁምን'? "

230 እርሱም ይላቸዋል፡ "እናንተ ያደረጋችሁት፡ እኔ አላውቀውም። እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ፡ አላውቃችሁም።" በእርግጠኝነት።

231 ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ “ደጁ ጠባብ፡ መንገዱም ቀጭን ነው፡ የሚያገኟትም ጥቂቶች ናቸው።” እየተነጋገርን ያለነው “ጥቂት” ስለተባለው ነገር ነው ምክንያቱም ያለነው ጥቂቶች ብቻ መሆን ያለበት የመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። ወንድሞቼ ሆይ፡ እባካችሁ፡ ተቀበሉት!

232 እዚህ ስለመቆሜ እንዲህ አታስቡ... ቢቀር ይሻለኛል... እንደ እኔ ቢሆን፡ እንደው—እንደው... እንደ እኔ፡ እኔም ከራሴ ጋር አመቻምቼ እንዲህ ባልኩ ነበር፡ “የአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ እንቅስቃሴን እንምረጥ፡ ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለን ሕብረት እናድርግ።” ይሁን እንጂ፡ ወንድሜ፡ ሆይ፡ ያን ባደርግ ወዮልኝ! ወዮልኝ! ከዚህ የበለጠ አውቃለሁና። እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ነገር በማድረጌ ወደ ገሃነም ይወስደኛል። አዎን፡ ወዳጄ። የሆነ ነገር ካለ... ምስክርነቴ ከህይወቴ ጋር ማተም አለብኝ፡ ማተም ይገባኛል፡ በቃ። በውስጤ የሆነ ነገር ስላለ፡ በአለም ከዚያ በላይ ሌላ ምንም ማድረግ አይቻለኝም።

233 ይህ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፡ እና ከእውነት ጋር መቆም አለብኝ፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይደግፈዋል። ድርጅቱ ይቃወሙታል፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ትክክል ነው ይላል። “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት ይሁን፡ የሱ ብቻ እውነት ይሁን።” እውነት ያ ነው፡ አለቀ፡ ከሱ ጋር ብቻ ቁሙ።

> ... **አደርጋቸዋለሁ... የሰይጣን ማኅበር:...** (መልካም።)... እነሱም ያውቃሉ... **ወደ እግርህ መጥተው:... እኔም እንደወደድኩህ...** ያውቃሉ።

> **የትዕግሥቴን** ቃል **ስለ ጠበቅህ፡ እኔ ደግሞ በሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው** ከ**ፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ፡...**

234 አሁን ተመልከቱ፡ ይህ እኔ የምናገረው የሜቶዲስት ዘመን እንዳልሆነ ለማሳየት፡ ግን፡ ተደራቢው ነው። ተመልከቱ! ለመስማት ዝግጁ ናችሁ? ሁላችሁ? አሁን በደንብ ስሙኝ፡

> **የትዕግሥቴን ቃል** ስለ **ጠበቅህ፡ እኔ ደግሞ በሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው እጠብቅሃለሁ** (ጥቂቶቹ ቅሪቶችን) **የፈተናው ሰዓት፡** ሲሆን...

235 ቤተክርስቲያን እንዲህ ትሆናለች በእነዚህ ድርጅት የምትጠቃለሉበት ጊዜ ይመጣል ወይም—ወይም... መቀበላችሁ—ወንድሜ መቀበላችሁ፡ የማይቀር ነው። በቃ። አንድም ትደራጃላችሁ ወይም የአውሬውን ምልክት ትቀበላላችሁ፡ ወይም... አንድም ታደራጇታላችሁ፡ ወይም ደግሞ የኃይማኖት ተቋም ትሆናለች (ይህም በእርግጥ እየመጣ ያለው የአውሬው ምልክት ነው)፡ ምክንያቱም ቦይኮት ነው። አያችሁ?

> **... ይመጣልና... በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ፡ በዓለም** ሁሉ **ላይ** ይመጣል**።**

> **እነሆ፡ በቶሎ እመጣለሁ፡ ማንም አክሊልህን** እንዳይ**ወሰድብህ፡ ያለህን** አጽንተህ ያዝ**።**

236 አሁን ይህ በጣም ታላቅ “ፈተና፡” ዓለምን ሁሉ ሊፈትን የሚመጣው የፈተና ሰዓት፡ ወደ መከራ ይቀየራል። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እናየዋለን። ወደ መከራ ይለወጣል፡ እናም መከራው በዌስሊ ዘመን አልመጣም። ታዲያ

እኛ በምን ዘመን ላይ ነን? ይህ ከፊት የተዘጋጀ "በር" ምንድነው? በዌስሊ እና በዚያ መካከል ነው... አሁን ቤተ ክርስቲያን እየሄደችበት ባለው ላይ; በርግጥ አሁን ገብታበታለችና፡ ይህም የሎዶቅያ ዘመን ነው። **እዚህ** ጋር የምትታየው አነስተኛ ሰፍራ ግን፡ ባለፋት ሰላሳ-አምስት፡ እና አርባ አመታት ውስጥ፡ "የተከፈተ በር" በመሆን ሊገቡ በሚመጡ ሰዎች ፊት የተዘጋጀች ነበረች፡ እግዚአብሔርም ቅሪቶችን ወስዶ በማህተም ይዘጋዋል። ያኔም ወደ ለብታ ይወስዳሉ እርሱም ከአፋ ይተፋቸዋል። ሥራው ቶሎ ይቋረጣል፡ ቤተክርስቲያን ትወስዳለች፡ እነሆም የክርስቶስ ተቃዋሚው ለጥፋት ይገባል። ይህ ነገር ከመላ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር፡ ፍጹም ልክ ነው። መልካም፡ አሁን።

237 እነሆ የሰነፎቹ ደናግሎች መምጣትም ይሄኛው ነው። እዚህ ላይ የመጨረሻው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ወደ ጰንጠቆስጤ የመጀመሪያ ክፍል እንደሚሸጋገር ያረጋግጣል፡ ወደሚመጣው ወደዚያ ወደ ታላቁ መከራ ይገባሉና... ይህም በዌስሊ ዘመን አልመጣም ነበር።

238 11 ኛ ቁጥር፡ መልካም፡ "የሕይወት አክሊል።" የ—11ኛው ቁጥር እንዲህ ይላል፦

> **እነሆ፡ በቶሎ እመጣለሁ፡...** (ምን? **አሁን** ፈጠን እንበል ከዚህ በኋላ፡ አያችሁ።)
>
> **እነሆ፡ እኔ...** ያለህን **አጽንተህ ያዝ** (በደንብ ጠብቀው)፡ **አክሊልህን ማንም ሰው** እንዳይወስድብህ።

239 "አክሊል" ምንድነው? አክሊል ምንድነው? ይህ ማለት—ማለት—ማለት... **አክሊል** ማለት "ግዛትህን—መያዝ" ነው። አክሊል ከተደረገብህ ንጉስ ነህ ማለት ነው። አያችሁ? እኛ የዘላለም ሕይወት አክሊል ሰንቀዳጅ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፡ ግዛታችንም ምድር ናት፡ "የእግዚአብሔር ካህናትና ነገሥታት አደርጋችኋለሁ።" ልክ ነው? እንግዲህ ይኸው ነው።

240 በአዲሲቱ ኢየሩሳሌምም፡ የምድር ነገሥታት ክብራቸውን በዚያች ከተማ በደንብ ያመጣሉ። ኦህ፡ ድንቅ ነው! እንግዲህ... መቀበል ከወደዳችሁ። አያችሁ፡ አክሊሎች አርጋችሁ፡ ልክ እንደ ከዋክብት ትደምቃላችሁ። እና ዳንኤል 12፡3 ላይ ለመጻፍ ከፈለጋችሁ፡ ሰለሱ ታላቅ የሆነ፡ በግሩም አገላለጽ ይገልጸዋል። ይሄን ለማየት ምናልባት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ይቀረናል። ዳንኤል በዳንኤል ምዕራፍ 12 ላይ፡ የተናገረውን፡ እዚህ ጋር እናገኘዋለን። መልካም። በመጀመሪያ ምዕራፍ 12 ላይ፡ እንጀምር፦

> **በዚያም ዘመን... ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል** (አያችሁ? ኦህ፡ ያ ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? )... **እንዲህ ይሆናል... ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ መስፍን፡ ይነሣል፡ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ፡** (ምንድነው? ወዲያውኑ **ከዚህ** ነገር በኋላ። ከመከራው!) **እንደ እርሱ** ያለ **ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፡ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ፡ እያንዳንዱ ይድናል።**
>
> **በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፡ እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት** (ወደ አክሊል)፡ **እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም** ጉስቍልና።

**ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል ይደምቃሉ፡ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም** ይ... **ደምቃሉ።**

241 ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ እነሆ "እክሊልህ፡" የዘለአለም ህይወት ድንቅ እክሊልህ ይህ ነው! የዘላለም ሕይወት እክሊል.

242 12ኛ ቁጥር፡ በፍጥነት ወደፊት... እና ከዚያ በኋላ ወደዚህ የምንቀጥል ይመስለኛል።

**ድል የነሣውን በአምላኬ ቤተ መቅደስ ውስጥ ዓምድ አደርገዋለሁ፡...**

243 አሁን ይህን በፍጥነት እናልፈዋለን ምክንያቱም አሁን አምስት ደቂቃ ወደፊት ወስጃለሁ። ጠዋት ላይ ግን ትንሽ መተኛት ትችላላችሁ፡ አይደል? እማ፡ አስተኚው። አንቺም ዘና ብለሽ ቁሚ፡ በርግጥ ፖፕን መቀሰቀስ ከባድ ነው። ይሁን እንጂ ትንሽ አስተኚው። ቀስ ብለሽ አላቂው፡ ቡና ከተደረገለት፡ ወይም የሆነ ነገር ሲያደርግ፡ ወዲያው ይነቃቃል።

**ድል የነሣውን በአምላኬ ቤተ መቅደስ ውስጥ ዓምድ አደርገዋለሁ፡...**

244 እሰኪ፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል ቃል በቃል እንመለከተዋለን። ትንሽ ትታገሱኛላችሁ፡ ትንሽ ብቻ? ሞቃታማ እንደሆነ አውቃለሁ፡ እናንተም እዚህ እንደሚሞቅ ታውቃላችሁ። ግን እንየው፡-

**... እኔ አደርገዋለሁ... ድል የነሣው በአምላኬ ቤተ መቅደስ ውስጥ ዓምድ አደርገዋለሁ፡...**

245 "ዓምድ።" **ዓምድ፡** ወይም "መሰረት።" በቤተ መቅደስ፡ ወይም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መሰረት። "የአምላኬ **ቤተ መቅደስ**፡" ወይም፡ "የአምላኬ 'ቤት'።" ዓምድ ነው፡ መሰረት ይሆናል። እነዚህ (በቁጥር 8) የሰሙትን ቃል ተቀብለው፡ ወደ መሠረት የተመለሱ ናቸው።

246 አሁን ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2፡19 ላይ፡ ኤፌሶን ቤተክርስቲያን እንመልከት። ወደ ኤፌሶን መመለስ አለብን፡ ታውቃላችሁ፡ መጀመሪያ ያ ነው። ትክክል ነው? እሺ፡ ጳውሎስ ወደ ነበረበት ወደ ኤፌሶን፡ እሱ ወዳቋቋመው ቤተ ክርስቲያን እንመለስ። እና አሁን የት እንዳለን እነይ። እሺ፡ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፡፡ አሁን ወደ ኋላ እንመለስ እና ያኔ መሰረቱ ምን እንደሆነ እንመልከት፡ እና በዚያ በመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን ጳውሎስ ሰለ መሠረቱ ምን እንደተናገረ እንመልከት። ለኤፌሶን ሰዎች ይናገራቸዋል፡-

**እንግዲህ ከእንግዲህ ወዲህ፡ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ፡ እንግዶች ወይም መጻተኞች አይደላችሁም።**

**መሠረት ላይ ታንጻችኋል...** (ሉተራን፡ ወይም የ—ወይም ባፕቲስት... አሁን፡ ቆይ፡ ቀላቀልኩት፡ አይደል? ኧረ-ኦህ።)

**ነገር ግን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፡ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡**

247 ሁሉም ነገር በበሩ በኩል ይገባል፡ በኢየሱስ! “ድል የነሣውንም ዓምድ አደርገዋለሁ።” በሌላ አነጋገር፡ የመሠረቱ አካል አደርገዋለሁ። “ምን እሰጠዋለሁ? ከመጀመሪያ የሐዋርያትንና የነቢያትን ትምህርት በርሱ ውስጥ አኖራለሁ፡ መገለጡንም እሰጠዋለሁ።” ነቢያት ስለ እርሱ ምን አሉ? እርሱ ድንቅ መካር፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ነው። ነቢያትም፡ ሐዋርያትም፡ የተናገሩት ይህ ነው። “እነዚህን የሰይጣን ማሕበሮችን ሁሉ ድል ነስቶ፡ ራሱን ነጻ አርጎ ወደ በሩ የሚመለከት፡ ዓምድ አደርገዋለሁ፡ በአምላኬ ቤት በቃሌ መሠረት ላይ አኖረዋለሁ።” ኦህ፡ ማይ! “በቃሉ ውስጥ በትክክል በምትቆዩበት መሠረት ላይ፡ በዚያ ዓምድ ውስጥ አኖረዋለሁ።” አሜን። ወንድሜ ሆይ፡ መልካም ነው፡ ደስ ብሎኛል። አስቂኝ ልሆንባችሁ እችላለሁ፡ ይሁን እንጂ... ደስ ብሎኛል። መልካም።

... **አደርገዋለሁ...** ድል ለሚነሳ... **በአምላኬ ቤተ መቅደስ ውስጥ ዓምድ አደርገዋለሁ፡ ወደ ፊትም አይወጣም፡**...

ያ ምንድን ነው? ዓምድ ከሆነ፡ ከእንግዲህ ወዲህ አይወጣም። ሙሽራ ነው! ትክክል ነው።

248 እንደ ኤፌሶን ዘመን፡ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ እንዳስተማራቸው... እስኪ፡ አንዴ ቆዩኝ። ዓምድ የምትሆኑ ከሆናችሁ... ወደ ሙሽራይቱ ከማለፋችን በፊት ላሳያችሁ የምፈልገው ሌላ ቃል አለኝ። አሁን፡ እሱ ዓምድ ከሆነ፡ ወደ ኤፌሶን ትመለሳላችሁ፡ ጳውሎስ ወደ ነበረበት ዘመን ትመለሳላችሁ። የኤፌሶን መልአክ፡ ጳውሎስም፡ የቤተ ክርስቲያን ጅማሬ፡ መሠረት፡ እንዲህ አስተማራቸው፡ “‘በኢየሱስ ክርስቶስ’ ስም በቀር በሌላ በማንም ስም የተጠመቃችሁ ከሆናችሁ፡ እንደገና መጠመቅ አለባችሁ አላቸው።” ትክክል፡ የሐዋርያት ሥራ 9 ላይ፡ ወይም 5:19 ላይ፡ ማለቴ፡ 19:5 እንጂ። በገላትያ 1፡ 8 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ “ከዚህ በተለየ መልኩ የሚያስተምር መልአክ ቢመጣ፡ የተረገመ ይሁን።”

249 እነሱ በቤተመቅደስ ውስጥ የነበረችው ሙሽራም ነበሩ። አሁን ወደ ራዕይ ምዕራፍ 7 እንሂድ፡ እና የራዕይ ምዕራፍ 7 ሙሽራ፡ እንደነበሩ እንይ።

250 አሁን፡ ምናልባት፡ እ—እኔ... እዚህ የምንናገረው፡ ስለ እስራኤል ቅሬታዎች፡ ስለ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ፡ እና ስለ ሌሎቹ ነው፡ ነገር ግን እስኪ—እስኪ ይህን አልፍ እንበለው እና ወደ ቁጥር 12 ወረድ እንላለን። የጴንጤቆስጤ ጉባኤ ነው፡ በሉት! ይህ ሕዝብ የነበረው... ኦህ፡ ተመልከቱ... እንግዲህ፡ እዚህ በ9ኛው ቁጥር እንጀምራለን ምክንያቱም የመጀመሪያው ለእስራኤል ነው፡ ከመካከላቸውም መቶ አርባ-አራት ሺህ የታተሙ ነበሩ፡ ይህም ነገ እናየዋለን።

እና... ከዚህም **በኋላ አየሁ፡ እነሆም፡ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል፡ እጅግ ብዙ ሕዝብ ነበሩ፡...**

251 አሁን፡ ከ4 እስከ 8 ያለው ስለ እስራኤል፡ እሱም ጃንደረቦች፡ የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች እንደሆኑ፡ አስታውሱ። ተመልከቱ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በጠዋት እናየዋለን። ስለዚህ፡ በዚያም አሥራ ሁለቱን ነገዶች፡ አተመ። ከይሁዳ ነገድ፡ አሥራ ሁለት አተመ፡ ከሮቤል፡ አሥራ ሁለት አተመ፡ ከጋድ፡ አሥራ ሁለት አተመ፡ ከሌዊ፡ እና ከዛብሎን፡ እና ከብንያም፡ አስራ ሁለት። የእስራኤልስ ነገዶች ስንት ናቸው? [ጉባኤውም “አስራ ሁለት፡” በማለት መለሰ።—አርታዒ።] እሺ፡

አሥራ ሁለት ጊዜ አሥራ ሁለት ስንት ነው? መቶ አርባ-አራት ሺህ። ሁሉም የእስራኤል ልጆች ነበሩ፡ ዮሐንስም፡ አይሁዳዊ ነበርና፡ ሁሉንም አወቃቸው።

> **ከዚህም ነገር በኋላ... እነሆ፡ ማንም ሊቈጥራቸው የማይችለው፡** እጅግ ብዙ፡ (እነዚህ ደግሞ ከአሕዛብ የመጡ ናቸው።) **ከሕዝብና:... ከነገድ፡ ከቋንቋም ሁሉ፡ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡ ነጭ ልብስም ለብሰው፡ የዘንባባንም ዝንጣፊዎች** በእጆቻቸው **ይዘው፡** በእግዚአብሔር፡ **እና... በበጉ ፊት ቆሙ፡**

252 እነዚያም ያኔ ሰማዕት የሆኑ ምስኪኖች ሰዎች ናቸው (በአንበሶች እና፡ በልዩ ልዩ ነገር የተበሉ ናቸው) ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የሚንጠባጠብ ነውና። ጭንቅላታቸዉን በየጎዳናዉ ላይ የተፈነከቱ እና ልዩ ልዩ ነገር የሆኑ፡ በሺዎች እና ሺዎች የሚቆጠሩ ህጻናት ልጆች፡ እነሆ በዚያ ይቆማሉ! ነጭ ልብስ ለብሰው፡ የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይይዛሉ። ኡህ፡ ማይ!

> **በታላቅም ድምፅ እየጮ**ሁ፡ **በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና፡** ለበጉ **ማዳን ነው፡ አሉ።**

> **... ማዳን በዙፋኑ ላይ** ለተቀመጠው **ለአምላካችን:...** ለበጉ፡፡

> **መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና፡ በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ** ዙሪያ **ቆመው ነበር:... በዙፋኑም ፊት፡ በግምባራቸው** ተደፉ... **ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡**

253 የጴንጤቆስጤ ስብሰባ ነው ብላችሁ ካላሰባችሁ፡ አዳምጡት፡

> **እንዲህ አሉ—እንዲህ አሉ፡ አሜን**፡ በረከትና:... **ክብር:... ጥበብም:... ምስጋናም:... ውዳሴም:... ኃይልም:... ብርታትም፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም** ለአምላካችን **ይሁን። አሜን።**

254 ዋው! የካምፕ ስብሰባ የነበራቸው ይመስላል፡ አይደል? ኧሃ-ሃህ።

> **... ከሽማግሌዎቹ** አንደኛው—አንዱ **መለሰልኝ፡ እንዲህ** ጠየቀኝ:... ወይም፡ **እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ** መጡ? **አለኝ፡**

“እንግዲህ፡ አንተ አይሁዳዊ ነህና፡ አስራ ሁለቱ ነገዶችን ታውቃለህ። እንግዲህ፡ እነዚህስ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? ነጭ ልብስ ለብሰዋልና፡ ከወዴት መጡ? የነ ብንያም እና ሌሎቹ ነገዶች የሉበትም። ታዲያ እነኚህ እነማን ናቸው? ”

255 ዮሐንስም እጅግ... ? ...

> **... ጌታ ሆይ፡ አንተ ታውቃለህ፡ አልኩት።** (“እኔ—እንደኔ እንደኔ! እ—እ... ” እያችሁ? ) **እርሱም** አለኝ፡ **እነዚህ ከታላቅ** መከራ የወጡት ናቸው፡ **ልብሳቸውንም አጥበው፡ በበጉ ደም አነጹ።**

> ስለዚህ... **በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት** አሉ፡ (በቤቱ ውስጥ) **ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩ**ታል፥ **በዙፋኑም ላይ** የተቀመጠው **በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።**

(ትንሽ ተርበው የኖሩ ይመስላሉ፡ አይደል?) **ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፡** (ክብር!) **ከእንግዲህም ወዲህ አይጠ**ሙም፡ **ፀሐይም ትኩሳትም ሁሉ፡** ከቶ፡ **አይወርድባቸውም፡**

**በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፡** ወደ **ሕይወትም... ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፡ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ...** ከዓይናቸው **ያብሳል።**

ይኸው፡ ሙሽራይቱ ይህች ናት። ኦህ፡ ማይ! እንዴት ድንቅ ነገር ነው! ሙሽራይቱ!

256 ስለዚህ አሁን እንደማያመልጠን እርግጠኞች እንድንሆን፡ አሁን እዚህ ጋር የተናገረውን እንይ፡ 12ኛው፡

**ድል የነሣው በአምላኬ ቤተ መቅደስ ውስጥ ዓምድ** ይሆናል፡ **እና...** ከእንግዲህም አይወጣም፡...

ሙሽራይቱ ከሙሽራው ጋር ቆማለች። ኦህ!

257 አቤት፡ አቤት፡ እንደው በውስጤ ያለውን በተረዳነው (በዚያ ላላው ለመጽሐፉ ነው)፡ በራእይ ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "የምድር ነገሥታት ሁሉ ክብራቸውን ወደ እርሰዋ ያመጣሉ።" ልክ እንደ... እነ ሌዊም ነገድ፡ የቀሩትም ሁሉ አሥራት ይሰጡታል፡ አያችሁ፡ ከአንዱ መባቻ ወደ ሌላው፡ ከሰንበት ወደ ሌላው ሰንበት፡ ሊሰግዱ ይወጣሉ። እንዴት ያለ ቀን ይሆናል! መልካም። "እኔም... " እንመልከተው እስኪ፡ "ከእንግዲህም ወዲህ አይወጡም።" መልካም።

**... በአምላኬ ቤተ መቅደሰ ውስጥ ዓምድ፡... የአምላኬንም ሰም በእርሱ ላይ እጽፋለሁ፡...**

258 እሺ፡ የእግዚአብሔር ሰም ማን ነው? ኢየሱስ። ማስታወሻ መያዝ ለምትፈልጉ (ትንሽ ዘግይተናል።)፡ "ኢየሱስ ነው!" ኤፌሶን 3:15 ላይ፡ "በሰማይና በምድር ሁሉም፡ በኢየሱስ ሰም ይጠራሉ፡" አያችሁ። መልካም። መልካም፡ አሁን። መልካም፡

**... የአምላኬም ከተማ ሰም፡ ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ** የምትወርድ፡ **አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ነው፡** በእሱ ላይ እጽፋለሁ... (ኦህ! ካያችሁ፡ ሁሉም ተመሳሳይ ሰም ነው፡ ቀድማችሁ መረዳት አለባችሁ። አያችሁ? አያችሁ?)... **የአምላኬ ከተማ ሰም... በእሱ ላይ እጽፈ**ዋለሁ፡...

259 "ከተማዋ።" ወደ ፊት በመቀጠል እንዲህ ይላል፡ "አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት።" አያችሁ፡ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ናት። "አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን በእርሱ ላይ አኖራለሁ።" አሁን፡ ሙሽራይቱ፡ ወይም ቤተክርስቲያን፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት። ሰንቶች ታውቃላችሁ? ቤተክርስቲያን ራሷ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ናት። ታምናላችሁ?

260 እስኪ እናረጋግጠው። ራእይ 21 ላይ፡ የምፈልገው ነገር፡ በዚያ ውስጥ ይመስለኛል። ምመልካም፡ እስኪ እናንተን ማሳየት እንድንችል እዚህ ጋር እንመልከተው። መጽሀፍ ቅዱስ ሲናገር "ሁሉን ፈትኑ፡" ይላልና፡ አያችሁ። አሁን፡ ራዕይ 21። ኦህ፡ ይህን በትክክል ሰሙ... ይህ... ይህን አዳምጡ፡ ይህች

የእግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ስም) አዲስ ከተማ ምን እንደ ሆነች ማየት አለባችሁ።

> **አዲስ** ሰማያት **እና አዲስ ምድርም አየሁ፡ ፊተኛው ሰማይና... ፊተኛይቱ ምድር** አልፈ**ዋልና፡ ባሕርም ወደ ፊት የለም።**
>
> **እኔም ዮሃንስ ቅድስቲቱም ከተማ፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፡ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፡ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።**

261 አዲሲቱ—አዲሲቱ ቤተክርስቲያን የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን ናት፡ ሙሽራ ናት። ሙሽራይቱ አህዛብ ናት፡ እና አሕዛብም ሰሙ አላቸው። ስለ ሰሙ ሲል ከአሕዛብ መካከል ሰዎችን ወሰደ። ታምናላችሁ?

262 ካላመናችሁ፡ የሐዋርያት ሥራ 15:14 ላይ ክፈቱ እና እወቁ። የሐዋርያት ሥራ 15:14፡ ማየት ከፈለጋችሁ አንድ ሴኮንድ ቆዩ፡ እንዲህ እናደርጋለን... ስለዚህ እናንተ... የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 እና 14 ኛ ቁጥር፡ እንደምናገኘው አምናለሁ። አሁን፡ ለመዝጋት ተቃርበናል። የሐዋርያት ሥራ 15 እና 14ኛው ቁጥር፦

> **እነርሱም ዝም ካሉ በኋላ፡ ያዕቆብ፡ እንዲህ ሲል መለሰ፡ ወንድሞች ሆይ፡ ሰሙኝ፡**
>
> **እግዚአብሔር ከአሕዛብ ለሰሙ የሚሆንን ሕዝብ ይወስድ ዘንድ፡ አስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን ተናገረ።**

ኧሃ-ሃህ። መልካም፡ ያቻትና። ኦህ!

263 አሁን በጣም እንደተጠጋነው የመጨረሻውም ክፍል እንዳገኘነው ይመስለኛል፡ እና ይህ እሱ ራሱ ነው በማለት እንዘጋለን።

> ... **በእርሱም ላይ የአምላኬን ስም፡ የአምላኬንም ከተማ ስም እጽፋለሁ፡**...

ሁሉም ያው ነው፡ ኢየሱስ፡ ኢየሱስ፡ ኢየሱስ። ሙሽራይቱም ኢየሱስን አገባች፡ ወይዘሪት ኢየሱስ ተብላ እንድትጠራ ያስችላታል፡ ወዘተ፡ አያችሁ።

264 ዛሬ ማታ በዚህ ሕንፃ ውስጥ አንዳንድ መልከ መልካም ሴቶች አሉ፡ በጣም ውቦች፡ ይሁን እንጂ ከእነዚህ ሁሉ የእኔ አንዷ ነች፡ እሷም በስሜ ትጠራለች። ተረድታችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ስሜን ተሸክማለች፡ ሙሽራይቱ**ም** እንዲሁ። መልካም፡

> ... **በእርሱ ላይ የአምላኬን ስም እጽፋለሁ፡... የምትወርደው፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት**... ወይም፡ **የአምላኬ ከተማ፡ እርሰዋም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት፡** ከእግዚአብሔርም የምትወርድ... **ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ፡ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።**

265 ይህን ብተወው ይሻለኛል፡ አይደል? መልካም። "እሱን" እንደሚል አስተውሉ፡ ነጠላ። አሁን ለመከለስ ያክል፡ አንድ ደቂቃ ወደ ራእይ 2፡17 ከተመለሳችሁ፡

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይስማ። ድል ለነሣው ከተደበቀ መና ይበላ ዘንድ እሰጠዋለሁ፡ ነጭ ድንጋይም እሰጠዋለሁ፡ በድንጋዩም ውስጥ** ከተቀበለው በቀር **ማንም የማያውቀው አዲስ ስም ተጽፎአል።**

266 አትወዱትምን? ድንቅ አይደለምን?

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
እሱ ወዶኛልና
መዳኔንም ገዛ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

267 ታውቃላችሁ፡ የሚቆራርጥ እና እንዲህ አይነቱ ወዘተ ጉባኤ ከተደረገ በኋላ በመንፈስ መዘመር እወዳለሁ። እናንተስ? ኦህ፡ በመንፈስ መሆን እንዴት ደስ ይለኛል። ቃሉ! አያችሁ፡ ቃሉ አሁን ወርዷል፡ አሁን የሚያስፈልገው ትንሽ እርጥበት ብቻ ነው። አያችሁ፡ ጥቂት ምስጋና፡ ወዲያውም መብቀል ይጀምራል፡ አያችሁ። ኦህ፡ አትወዱትም ወይ? እጆቻችንን አንስተን እንዘምር፦

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
እሱ ወዶኛልና
መዳኔንም ገዛ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

268 ኦህ፡ አንገታችንን ደፍተን እንዲህ እንበል፦ "አባት ሆይ፡ እንወድሃለን። እንወድሃለን። አቤት፡ እንዴት እንደምንወድህ! ጌታ ሆይ፡ እጅግ፡ እናመሰግንሃለን። አቤቱ፡ ም—ምስኪኑ የሰው ልባችን በውስጣችን የሚሰማንን ሊገልጽ አይችልም፡ በገዛ ደምህ አጥበኸናልና። ጌታ ሆይ፡ መጻተኞች ነበርን። እኛም—የዓለምን ነገሮች የምንወድ፡ እና ሁላችንም—በዓለም ነገሮች ሁሉ ውስጥ የተበላሸን ነበርን፡ በጸጋህ ወርደህ እኛ በነበርንበት የኃጢአት ማጥ ውስጥ ውድ ቅዱሳን እጆችህን ዘረጋህልን፡ አወጣኸን፡ መረጥከን፡ አጠብከን፡ አነጻኸን፡ አዲስ መንፈስ በውስጣችን አኖርክልን፡ ከላይ ያለውን እንድንሻ አደረግከን። ጌታ ሆይ፡ እጅግ እንወድሃለን!"

269 ጌታ ሆይ፡ በዚህ በተታለለው ዘመን፡ በዚህ ኦኣለም ውስጥ የቀረ ነገር የለንም። ዕዓለም የቀራት ነገር የለም፡ የዘመን ፍጻሜ—ሆኗል—ፍጻሜ ነው። በመጽሀፍ ቅዱስ እንዳየነው፡ ዘመናት ሁሉ አልፈዋል። በፍጥነት ለመሄድ፡ ፍጻሜ ላይ ደርሰናል። በቅርብ ኢየሱስ ይመለሳል። አምላክ ሆይ፡ ዝም አታሰብለን፡ ልባችን አቀጣጥለው። ታላቁ ቅዱስ ጳውሎስ ዛሬ ማታ እዚህ ቢገኝ እና ነገሮችን በሁኔታው ቢያይ ምን ያደርጋል፡ ብዬ እሰባለሁ? ያኔ እሱ... ያ ሰው፡ ሳይነጋ እንደ ማታ ቢያሰሩትም እንኳ፡ ሕዝቡ ስለ ጌታ መምጣት እንዲዘጋጁ ይነግራቸው ዘንድ በወጣ ነበር።

270 ጌታ ሆይ፡ በዚህች ሰዓት፡ የታመሙ ብዙዎች እንዲጸለይላቸው የጠየቁ ብዙ መሃረቦች እዚህ አሉና። አባት ሆይ፡ ሁሉንም እንድትፈውሳቸው እጸልያለሁ። እውነት እንደሆነ በማይሳሳት አገልግሎትህ ያረጋገጥከው አካል እንደሆነ እናውቃለን፡ "አማኙን በሚከተሉ ምልክቶች።" ከጳውሎስ አካል መሀረብና ልብስ ወስደው ወደ ድውዮች ይልኩ ነበርና፡ ርኩሳን መናፍስትም

ይወጡ ነበር፡ ሕዝቡም በሕያው እግዚአብሔርን ሰላመኑ ይፈወሱ ነበር። አባት ሆይ፡ በፊትህ ሳቀርባቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ ዛሬም ያንን አድርግልን።

271 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ነፍሳችንን በእጅህ እንድትይዝ እጸልያለሁ፡ “ጠባሳ እና የፊት መጨማደድ ወደሌለባት ቤተ ክርስቲያን እንደምትመጣ” ተናግረሃልና፡ እጠበን፡ ተኩሰን። የመንፈስ ቅዱስ ትኩስ ካውያ መጨማደዳችን ሁሉ ረግጦ ያሰወግድልን፡ እኛም ስለ ሰው ልጅ መምጣት በመጓጓት ተዘጋጅተናል።

272 አባት ሆይ፡ አሁንም፡ በረከትህ በላያችን ያርፍ ዘንድ እንጸልያለን። አባት ሆይ፡ በአምልኮአችን ተገኝ። እናመልክሃለን። ዛሬ ማታ ቆመን ልባችንን እንሰጥሃለን። እኛ...

60-1210 የፊልደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው ።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org